# ኒኦ—ናችራሊዝም ፤ ለካፒታሊዝምና ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የሚስማማ የሕግ ፍልስ ፍና ስለመፍጠር

በኤም ኤ ኢንቱሚ *

## መግቢያ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ « ፍትህ » ፣ ትክክለኛ አስተሳሰብ (  ሪዝን ) ፣ « የተፈጥሮ ሕግ » ፣ « የተፈጥሮ መብቶች » ፣ ወዘተርፈ የሚሉት የተፈጥሮ ሕግ ጽንሰ—ሃሳቦች ለአጠቃላይ የሕግ ቲየሪ ዋና መሠረት እንዲሆኑ የቡርዠዋ የሕግ ሊቃውንት እያንሠራሯቸው ነው ። የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና የጥንት ሥፍራውን እንዲይዝ የሚደረገው ይህ ጥረት ፣ በምዕራቡ ዓለም ተሰሚነት ባላቸው በእነኻርት ፣ ቦዴን ሃይመርስ ፣ አንተራቬ ፣ ፉለር ፣ ሮስና ፣ ሮውልስ ግንባር ቀደምትነት የሚመራ ነው ።[1] በአፍሪካም በአንዳንድ ክልሎች በቅኝ አገዛዝ አማካይነት በገባው የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ምክንያት ፣ የጊዜው የሕግ አመለካከት ለተፈጥሮ ፍልስፍና በሚደረግ ከፍተኛ ጉጉት ተውጧል ። ለዚህም ማስረጃው በተፈጥሮ ፍልስፍና መርሆችና ጽንሰ—ሃሳቦች የታጀሉት የብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ሕገ—መንግሥቶችና ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ሥራዎች በአንዳንድ የሕግ ኰሌጆች እንደመደበኛ የመማሪያ መጻሕፍት እንዲያገለግሉ መደረጋቸው ነው ።[2]

የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ለብዙ ምዕተ—ዓመታት ለመቆየቱና ዛሬም ባለው የሕግ ፍልስፍና ላይ ብዙ ተጽዕኖ እያሳደረ ስለመሆኑ ብዙ ምክንያቶች ሊሰጡ ይችላሉ ። አንዳንዶች ፣ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናን « ዘለአለማዊነት » እና « የማይሞት መንፈስ » ለማንሠራራቱ እንደዋና ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ ።[3] አንድ ደራሲ « የተፈጥሮ ሕግ በፖዘቲቭ ሕግ ውስጥ እንዲገባ ካልተደረገ የሕጉን ላሕይ ለመምጠጥ እንደሚያስፈራራ በክፍል ውስጥ እንደሚያንዣብብ መንፈስ ይመስላል »[4] ሲሉ አስቀምጠውታል ። ሌሎች ምርምሮች ደግሞ ፣ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናን « ፍጹም » መርሆች « ዘላለማዊነት » ና « ሁለንተናዊ » ተግባራዊነት ይጠቅሳሉ ።[5] አለበለዚያ ስለሕግ ክስተት አጥጋቢ » ማብራሪያ መስጠት ያልቻለውን « የቪየናው ትምህርት ቤት » የፈጠረውን ኖርማቲቪዝም በመቃወም የተፈጥሮ ሕግ ቲየሪዎችን አጠቃላይ « ረቂቅ » ፈርጆች ( አብስትራክት ካቴጐሪስ ) የሚመለከት ሰበካ ይደረጋል ።[6]

የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና እንደገና ማንሰራራት ከላይ በተጠቀሱት ጥልቀትና ምጥቀት በጎደላቸው አነጋገሮች ምክንያት ነው ብሎ ለማሰብ በጣም ቀላልና ለማመንም የሚገፋፋ ነው ። በርግጥ ዘመናዊው የቡርዠዋ የሕግ ፍልስፍና ከኖርማቲቭ ፖዘቲቪዝም ለማፈንገጡ የኖርማቲቭ ፍልስፍና ጉድለቶችና ሳይንሳዊ መሠረት ማጣት እንደዋና ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ ። ይሁን እንጂ ፣ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናን እንደገና ማንሠራራት በነዚህ ሃሳባዊ አመለካከቶች ለማስረዳት መሞከር ስህተት ነው ። እንዲህ ዓይነቱ አገላለጽ ፣ ቁሳዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች በሕግ እድገት ላይ ያላቸውን ሚና አያስረዳም ። እንዲያውም ፣ እንዲህ ዓይነቱ አገላለጽ በተሳሳተ መንገድ ሕግ ወይም የሕግ ቲየሪ በአቀንቃኞቹ

አእምሮ አማካይነት ራሱን ከሶሻልና ከኢኮኖሚ ኃይሎች በላይ ከፍ ለማድረግ ይችላል የሚል አመለካከት ያሳድራል ። [7]

የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ዳግም የተወለደበት ቁሳዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች በሳይንሳዊ ዘዴ በጥልቀት ሲመረመሩ ፣ የዳግም ልደቱ መንሥኤና ይዘት የፖዘቲቪዝም ጉድለት ወይም የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ቅዱስ ባህሪ ( ቨርቹ ) አለመሆናቸውን መገንዘብ አያዳግትም ። በተቃራኒው ፣ የክስተቱ መንስኤና ይዘት የሚገኘው በካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት ውስጥ ነው ። ስለዚህ ፣ መንስኤውን ቁልጭ አድርጐ ለማሳየት ይህ ጽሑፍ በተለያዩ የካፒታሊዝም የእድገት ደረጃዎች ውስጥ በአእምሮ ሥራና በቁሳዊ ምርት መካከል የነበረውን ነባራዊ ዝምድና በጥልቀት ይመረምራል ። ይህንንም ስናደርግ ዓላማችን ወደተፈጥሮ ፍልስፍና ዳግም ልደት የመሩትንና ስለሕግ ያለውን አመለካከት ሊለውጡ የቻሉትን ክስተቶች ለይቶ ማመልከት ይሆናል ። ይህም በቅኝ አገዛዝና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፣ እንዲሁም በተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና መካከል እጅግ የተቀራረበ ግንኙነት መኖሩን ለማሳየት ይህ ጽሑፍ የሚያደርገውን ጥረት ያቃልልልናል ። ይህን ካደረግን በኋላ ማህበራዊና ርዕዮተዓለማዊ ይዘቱን ለማስረዳት ፣ የዘመናዊ የተፈጥሮ ሕግን ፍልስፍና ቲዮሪያዊ መርህና ረቂቅ የሕግ ፈርጆችንም ቀረብ ብሎ ለመመርመር ጥረት ይደረጋል ። ምክንያቱም የተፈጥሮ ሕግን ርዕዮተ—ዓለማዊ አቋምና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሳሪያነቱን ፣ እንዲሁም ፍትህ አልባው ሥርዓታችን እንዳለ እንዲቆይ ለማድረግ በመሳሪያነት ማገልገሉን ፣ ቁልጭ አድርጐ የሚያሳየው ይህ ይዘቱ ነው ።

## 1. የሕግ ፍልስፍና ዕድገት በካፒታሊስት ኅብረተሰብ

### /ሀ/ የተፈጥሮ ሕግና የካፒታሊዝም እንሳስ

የካፒታሊዝም ዕድገት ቁሳዊ መሠረቶች ፤ በ16ኛውና በ17ኛው ምዕተ—ዓመታት በምዕራብ አውሮፓ በንግድ መስክ የተካሄዱት አብዮቶች ናቸው ለማለት ይቻላል ። በሌላም በኩል ፣ ከንግድ አብዮት ጎን ለጎን የተካሄዱ መልክአ ምድራዊ ግኝቶች የሸቀጣ ሸቀጥ ምርትን ፣ የምርት ልውውጥን ፣ ኢንዱስትሪያዊ እንቅስቃሴን ፣ የባህር ላይ ጉዞንና የንግድ ወረትን ( ካፒታል ) ዕድገት አፋጥነዋል ። ከፊውዳሊዝም ወደካፒታሊዝም በተደረገው ሽግግር ውስጥ ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ምክንያቶች ዋነኞቹ እነዚህ ናቸው ። [8] እነዚህ የካፒታሊስቱ ሥልተ—ምርት የመጀመሪያዎቹ ዘመናት ፣ የማምረቻ መሳሪያዎች በጥቂቶች እጅ የሚሰበሰቡበትን ማህበራዊ ሁኔታዎች በመፍጠር ፣ ሥራን በማህበራዊ ደረጃ በማደራጀት ፣ በገንዘብ ቁጠባ ( ሴቪንግስ ) እና በኢንቨስትመንት ፣ እንዲሁም « ለነጻ » ገበያ ኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ የሆነውን የዓለም ገበያ በመፍጠሩ ላይ ያተኰሩ ነበሩ ። [9]

ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ፣ ግለሰቦች ቀስ በቀስ « ጨቋኝ » ከሆነው ከሃይማኖታዊ ወይም ከተቋማዊ ( ኢንስቲቱሽናል ) የበላይ ጠባቂነት በመላቀቅ ፣ መሬትን በግል የሚይዙበት ፣ ሥራ የሚደራጅበት ፤ የሸቀጥ ምርት ልውውጥና ክፍፍል ፣ የጉልበት ዋጋ ክፍያና ሌሎችም ንግድና ገንዘብ ነክ እንቅስቃሴዎች በሕግ ታውቀው የሚካሄዱበት ሁኔታዎች መፈጠር ነበረባቸው ። ከታሪክ አኳያ ሲታይ ፣ እንዲህ ዓይነቱን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ መፍጠር የአውሮፓው የቡርዣዋ መደብ አባላት ራሳቸውን ከፊውዳሎች ጫና ለማላቀቅ ያደረጉት ትግል

አካል ነው ። ጥቅማቸውን በሕግ ከለላ ለማስጠበቅ መሠረታዊና አስፈላጊ ማህበ
ራዊ ሁኔታ ነው ተብሎ የታመነበትም ፣ ንብረትን በግል የመያዝ መብት እና « የው
ል ነጻነት » አግባብ ባላቸው የወንጀለኛ መቅጫና የከውል ውጭ አላፊነት ድን
ጋጌዎች እንዲደገፉ ማድረግ ነበር ።

ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስም የማይደፈረውን የግል ንብረት መብትን ፣
እያንዳንዱ ግለሰብ ያለውን የነጻነት መሠረታዊ መብቶችን ፣ ነጻነትን እና እኩ
ልነትን የሚሰብኩ ቲየሪዎች እና የግሮሺስ እና የነሆብስ ፣ ሎክና ፣ ሩሶን የመሳ
ሰሉ የ18ኛው ምዕተ—ዓመት ፈላስፋዎች የተፈጥሮ ሕግ አስተሳሰቦች ሁሉ ፣
የግል ባለሀብቱን ከማንኛውም ቁጥጥር ነጻ ለማውጣት በሚደረገው ጥረት ዓይነ
ተኛ መሳሪያዎች ሆነው ተገኙ ። ግሮሼስ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናን ምድራዊ ሥጋ
በማልበስ የተፈጥሮ ሕግ ምንጭ ( በጥንት ምሁራን ሲነገር እንደኖረው መለኮት
አለመሆኑን ) እና የሰው ተፈጥሮ መሆኑን ፤ ያለምንም መለኮታዊ ኃይልም የተ
ፈጥሮ ሕግ ሊሠራ እንደሚችል ተናገረ ።[10] ሆብስ ደግሞ የግለሰቦች ፈቃድ ከቁ
ጥጥር መላቀቅ የተፈጥሮ መብትና የውል ነጻነት መሠረት ነው ሲል ለጉዳዩ አጽ
ንኦት ሰጥቶታል ።[11]

ሎክ ፣ በታወቀው የሶሻል ኮንትራክት ቲየሪው ፣ የግል ንብረት መብቶችን
ክስተት ( የካፒታሊስት የምርት ግንኙነትን ) መለኮታዊ ባህሪ ያጎናጽፈዋል ።
« እምላክ በፈቃዱ ሰው ምድርን እንዲገዛና ላቡን እንዲያፈስባት አዟል ፣ » ለዚህ
ትዕዛዝ ምላሽ በመስጠት መሬትን የሚያርሳት ሁሉ በማንም ሊነጠቅ የማይ
ችል ፍሬ ይሰበስባል » በማለት ክርክሩን ቀጠለ ።[12] ሎክ የግለሰብ ነጋዴን
ንብረት ከፊውዳል ቁርኝት ለማላቀቅ የሚጠቀምበት ዘዴ የሚደነቅ ነው ። ምርት
የአንድ ሰው ወዝ ፍሳሽ ነው ፤ የሚለውን አባባል በማጠናከር ምርት እና አም
ራች የማይነጣጠሉ አንድ አካልና አንድ አምሳል ናቸው ይላል ። የዚህም ውጤት
ይላል ሎክ ፣ « የግል ንብረት መብት ( « ንብረት » የሚለውን ቃል ሰውንና የም
ርት መገልገያ መሳሪያዎችን አቅፎ እንደሚይዝ አድርጎ ይጠቀምበታል ) ከሕግና
ከኅብረተሰብ በፊት የነበረ ስለሆነ ፣ ይህንን መብት ሁለቱም « ማክበር » አለባ
ቸው ። » ሩሶም የነጻነትንና የእርነትን መርሆ በማስተጋባት ነፃነትና እኩልነት
ከሰው ተፈጥሮ የማይነጠሉ መብቶች ናቸው ይላል ።[13]

ይኸ የአመለካከት ባህል ከ « ሕግ የበላይነት » ( ሩል ኦቭ ሎ ) ጋር የጠበቀ
ዝምድና እንደነበረው በቅንፍ ( ፓረንተሰስ ) ውስጥ ሊጠቀስ የሚችል ነጥብ ነው።
የዚህን ዶክትሪን ይዘት ለማስረዳት ሎክ የሕግን ምናብ ( ኢሜጅ ) በአጥር
ያስመስለዋል ። የሎክ አጥሮች ( ፌንስስ ) የግለሰብን እንቅስቃሴ ክልሎች በታ
ወቁ ሕጎችና ደንቦች በመከለል መብትና ግዴታዎችን ለይተው ያሳውቃሉ ።
እነዚህ በአጥር የተመሰሉ የሕግ ምናቦች የአንድን ሰው ንብረት ከሌላው ይለ
ያሉ ። እንዲሁም ፣ ግለሰብን ከመንግሥት ተጽዕኖ በመጠበቅ መንግሥት ራሱ
የሕግ ተገዢ እንዲሆን ያደርጋሉ ።[14] ይህ « የሕግ የበላይነት » ( ሩል ኦቭ ሎ )
የተሰኘው አስተሳሰብ የራሱ የሆነ ክልል ያለውና « በገለልተኝነት » የሚገኝ
መሆኑን መገንዘቡ ትምህርታዊነት አለው ።

የቡርዠዋ የሕግ ምሁራን የተፈጥሮን ሕግ ፍልስፍና ምድራዊ ሥጋ በማል
በስ ለቡርዠዋ መደብ ወደ ሥልጣን ‹ኩርቻ መወጣጫ እንዲሆነው የለውጥ ፈላ
ጊዎች ፍልስፍና አደረጉት ። የፊውዳሉ ሥርዓተ—ማህበር ከተንኮታኮተ በኋላ ፣
ነጻ ውድድርና ነጻ ገበያ የጊዜው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሕግ በመሆን ፣ በቡር
ዠዋ መደብ የፖለቲካ ቁጥጥር ሥር የግለሰብ ነጻነትና የውል ነጻነት ዋስትና ለመ
ሆን በቁ ።

/ ለ / ሊጋል ፖዘቲቭዝም እና የካፒታሊስት ሕጋዊነት

በ18ኛው ምዕተ—ዓመት በተፈጥሮ ሕግ ምሁራን የተሰበኩት ነጻነት ፣ እርነት እኩልነት ፣ ወዘተ የሚሉት መርሆች ፣ በ19ኛው ምዕተ—ዓመት መባቻ ላይ በመስፋፋት ላይ በነበረው በካፒታሊዝም ጥላ ሥር የቡርዠዋ ሥርዓትን የበላይነት አረጋገጡ ። ካፒታሊዝም የተቀዳጀውን ቁሳዊ ፣ መንፈሳዊ ፣ እና ርዕዮተ—ዓለማዊ የበላይነት በይበልጥ ለማጎልበት ቆርጦ ተነሳ ። ለዚህም የበላይነት ማረጋገጫ መሳሪያ ሆኖ የተገኘው ሊጋል ፖዘቲቭዝም ነበር ። ሊጋል ፖዘቲቭዝም ነጻነት ፣ ፍትሕና እኩልነትን የመሳሰሉ ጽንሰ—ሃሳቦችን ወደ ሕግነት ደረጃ በማሳደግ ፣ « ሕጋዊ መንግሥት » ( ሊጋል ስቴት ) የተሰኘ ጽንሰ—ሃሳብ በመፍጠር ፣ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና መሠረት ሁሉ ራሱ መንግሥት ነው ሲል አስተማረ ። ቀደም ሲል በነበረው የተፈጥሮ ሕግ አስተሳሰብ መሠረት የመንግሥት ሥልጣን ምንጭ የእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም « አጠቃላይ የሕዝብ ፈቃድ » መሆኑ ቀርቶ ፣ በሊጋል ፖዘቲቭዝም መንግሥት እንደ አንድ ራሱን የቻለ ግብና ሉዐላዊ ( ሶቨርይን ) ሆኖ ቀረበ ። መንግሥት ለሚለው ዶክትሪን የዛሬ መልኩን ባጎናጸፈው በኦስትን አስተሳሰብ ፣ መንግሥት ራሱ በራሱ የሥልጣን ሁሉ ምንጭ ( ሉዐላዊ ) ስለሆነ ሥልጣኑ በምንም ዓይነት ሕግ ሊገደብ አይገባውም ። [15]

ይህ መንግሥት የሚለው የፖዘቲቭዝም ዶክትሪን ፣ ሕግን በኅብረተሰቡ ውስጥ ካለው ነባራዊ ግንኙነት በመገንጠል ፣ ራሱን ሊጋል ፖዘቲቭዝምን እንድ የሕግ ቲዮሪ አደረገው ። በተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና የሰውን መብቶች የማወቁ ሁኔታ የሕግ ሁሉ መሠረት የግለሰብ ፈቃድ ነው ፤ ወደሚል መደምደሚያ ደርሶ ነበር ። ይህ ለቡርዠዋ ግንባታ ሕጋዊ መሠረት የነበረው ሃሳብ ማህበራዊነቱ የተገለጸው ፣ ነጻነቱን በተጎናጸፈው ግለሰብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነበር ። የግለሰብ ነጻነትና በጊዜው የነበረው ነጻ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ፣ ሕግንና ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያስተሳስር ድልድይ ሆነ ። ይሁን እንጂ ሊጋል ፖዘቲቭዝም የሕዝብን ፈቃድ በመንግሥት ኃይል በመተካት ኃይልን ( ማስገደድን ) የሕግ መሠረት አድርጓል ።

ከታሪክ አንጻር ሲገመገም ፣ ይህ የአስተሳሰብ ለውጥ የካፒታሊዝም ኢምፔሪያሊስትነት የእድገት ደረጃ መጀመሩን አረጋገጠ ። የማምረቻ መሳሪያዎችን በማሻሻል የተገኘው ከፍተኛ ውጤት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን በእጥፍ ድርብ አሳደገው ። ዋነኛ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሆኖ የቆየው የሸቀጥ ምርት ወደ ከፍተኛ የፋይናንስ ካፒታል ክምችትና ምንጊዜም እየጨመረ ወደሚሄድ የጥሬ ሀብት ፍለጋ እሽቅድድም አመራ ። ይህ የጥሬ ሀብት ፍለጋ ለመዋዕለ ንዋይ ( ኢንቨስትመንት ) ከሚደረገው ሩጫ ጋር በመደመር ካፒታሊዝም ገበያ ለመፈለግ ወደ ሁሉም የዓለም ክፍል ክንፉን እንዲዘረጋ አስገደደው ። [16] አፍሪካን ለመቀራመት የተደረገው ዘመቻና አፍሪካ ለልዩ ልዩ የአውሮፓ አገሮች የኢኮኖሚ ክልል እንድትሆን ያደረገው የ1884/85 የበርሊን ጉባኤ በዚህ ታሪካዊ ወቅት የተከናወነ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው ። [17] ስለዚህ ፣ የዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ዋነኞቹ መለያ ጠባዮች የሸቀጥ ማራገፊያ ገበያዎች እና የማይነጥፍ የጥሬ ሀብት ምንጭ የሚሆኑ ቅኝ ግዛቶችን መፍጠር ነበር ተብሎ ሊጠቃለል ይቻላል ። በቅኝ ግዛቶች የሚኖሩትን ሕዝቦች ለባርነትና ለረቀቀ ብዝበዛ መዳረግም ሌላው የዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ዋነኛ ገጽታ ነበር ። እነዚህ ቅኝ ግዛቶች ሊያዙ የቻሉትም ምዕራባውያኑ ካፒታሊስት መንግሥታት በነበራቸው እጅግ ከፍተኛ የፖለቲካና ወታደራዊ የበላይነት ምክንያት ብቻ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ነው ። ስለዚህ ፣ ኃይል የመንግሥት መሠረትና የጥንካሬውም ምንጭ ሆነ ። ቀጥሎም

ኃይልን የሕግ መሠረት በማድረግ ፣ ሊጋል ፖዘቲቭዝም የቡርዠዋው መንግሥት የሚወስዳቸውን የኃይል እርምጃዎች ሁሉ ሕጋዊ ለማሰኘት በመሳሪያነት አገለገለ ።

ይሁን እንጂ ፣ ሊጋል ፖዘቲቭዝም ተቀዳጅቶት የነበረው የበላይነት ተጽዕኖ ዕድሜው አጭር ነበር ። በ20ኛው ምዕተ—ዓመት መባቻ ላይ ሊጋል ፖዘቲቭዝም የነበረውን ተደማጭነት ማጣት ጀመረ ። አስትን የቀመረው የሕግ አስተሳሰብ ኬልሰንን በመሰሉ ቴክኖ ጁሪስቶች ከፍተኛ ለውጥ ተደረገበት ። በእርግጥ ፣ በኬልሰን ያልተነካካ የሕግ ቲዮሪ ይዘት ፖዘቲቭዝም በተለያየ ገጽታው በአጠቃላይ የሕግ ቲየሪ እና በልዩ ልዩ የሕግ ዘርፎች ውስጥ ብቅ ብቅ ማለቱን አሁንም አላቋረጠም ። ይህን ሁለንተናዊ ኖርማቲቪስት የሆነና ፎርማሊዝም ገንኖ የሚታይበትን « የሕግ አልጀብራ » ለመፍጠር የሚደረገውን ሙከራ የምዕራቡ ዓለም የሕግ ምሁራን ሳይቀሩ አውግዘውታል ።[18]

## ሐ/ ሶሲዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስና የካፒታሊዝም ርዕዮተ—ዓለማዊ ቀውስ

ሶሲዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ብቅ ማለት የጀመረው በ19ኛው ምዕተ—ዓመት አጋማሽ ላይ ዌበር ፣ ዱርኬይም ፣ እና ኤንሪትን የመሳሰሉ ደራሲያን የሕግን ሶሲዮሎጂካዊ መሠረት ፈልፍሎ ለማውጣት ሙከራ ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ ነው ።[19] ይሁን እንጂ ፣ እስከ 20ኛው ምዕተ—ዓመት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ድረስ በምዕራቡ ዓለም የሕግ ሳይንስ ውስጥ ተደማጭነትና ተከታይ ያለው የሕግ ቲየሪ ሊሆን አልቻለም ። ይህ ዕድገት ካፒታሊዝም ሁለንተናዊ ክስተት ለመሆን ከበቃበት ማህበራዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው ። በእርግጥም ከቅኝ ግዛቶች መፈጠር በኋላ የቅኝ ግዛት ቀያሽ መሐንዲሶች ዋና ፍላጐት ቅኝ ግዛቶችን የቻሉትን ያህል መዝረፍና የዘረፉትን ሀብትም ወደየሀገሮቻቸው መላክ ነበር ። ቅኝ ግዛትንና የኢኮኖሚ ክልልን ለማስፋፋት በቀንደኞቹ ካፒታሊስት አገሮች መካከል የተደረገው የእብደት ሩጫና ትንቅንቅ ዓለምን ከዚያ በፊት አይታ ወደማታውቀው ሰቆቃና እልቂት — አንደኛው የዓለም ጦርነት—ውስጥ ከተታት ።[20] ካፒታሊስት በሆኑት አገሮች የተከሰቱት ማህበራዊ ሁኔታዎች ፣ ሕግን የማስከበርና ቅኝ ግዛቶችን የማስተዳደር ችግሮች ፣ የቡርዠዋ መንግሥታትን አፋጠጧቸው ። ለግዛቱ መፈጠር መሳሪያ የሆነው ፖዘቲቭስት የሕግ ሥርዓት ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ችግሮች ቦታ አልነበረውምና የተፈጠረውን አዲስ ክስተት ሊያቅፍ አልቻለም ።

ሶሲዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ የሕግን ማህበራዊ መሠረት ለማብራራት ባለው ጽኑ ፍላጐት ምክንያት ፣ ለነኝህ ችግሮች ምላሽ ለመስጠት እንደ ዋነኛ የሕግ ቲየሪ ብቅ አለ ።[21] የዚህ አስተሳሰብ ቀንደኛ አራማጅ የነበረው ሮስኮ ፓውንድ ፣ ሕግ በመጻሕፍት ውስጥ እንደሚገኝ የውጤቶች ስብስብ ሳይሆን ፣ እንደ ሕጋዊ ሥርዓት ( ሊጋል ኦርደር ) እና ሂደት መቆጠር ያለበት መሆኑን አበክሮ አስገነዘበ ። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ፣ ሕጋዊው ሥርዓት ( ሊጋል ኦርደር ) መንግሥት በተቀነበባረ መንገድ ኃይልን በሥራ የሚተረጉምበትን ሁኔታ ሲወክል ፣ ሕጋዊው ሂደት ( ሊጋል ፕሮሰስ ) ደግሞ የፍትህ አስተዳደርንና ዳኝነት በሕጎችና በአዋጆች መሠረት የሚከናወኑበትን ሁኔታ ያመለክታል ።[22] ሶሲዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ለካፒታሊስት ሕጋዊነት ( ኃይል ) ትክክለኝነት ማረጋገጫ ( ጀስቲፊኬሽን ) በመስጠት ፣ የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅሞች ለመንከባከብና

እንዳሉ ለማቆየት ከመፈለጉም በላይ ፣ የካፒታሊስት ሕግና ሥርዓት የሚከበሩበትንና ቅኝ ግዛቶች የሚስተዳደሩበትን መፍትሄም ለማቅረብ ሞክሯል ።

ሕግ ከማህበራዊ ግንኙነቶች ሲነጠል የሚፈጠሩትን ማህበራዊ ችግሮች በማስረዳት በሕጎችና ደንቦች ላይ ብቻ ፍጹም የሆነ እምነት ማሳደሩ ትክክል አለመሆኑን ለማሳመን ሶሲዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ያደረገው ጥረት ተሳክቶለት ነበር ። ይሁን እንጂ ፣ ሶሲዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ስለሕግና ሕግ ሊኖረው ስለሚገባው የተወሰነ መልክ ያለው አስተያየት ፍጹም አፍራሽ በመሆኑ ምክንያት ፣ የሊጋል ፖዘቲቪዝምን ጉድለቶች ሊያስተካክል አልቻለም ። ማህበራዊውን ምርት በግል የመያዝ ቀጥተኛ ውጤት የሆነው ወዝ አደሩን ከምርቱ የመነጠሉ ሁኔታ ፣ የካፒታሊስት ሥርዓት ዓይነተኛ ማህበራዊ ችግር እንደሆነ ሊቀጥል ችሏል ። እነዚህ ማህበራዊ ችግሮች በካፒታሊስቱ ዓለም ብቻ ሳይወሰኑ ፣ እንዲያውም በአስከፊ ገጽታቸው በቅኝ ግዛቶችም ጭምር መከሰታቸው ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ነው ። በአንድ ወቅት በእንግሊዟ ንግሥት ፣ በፈረንሳዩ ንጉሥ ፣ በጀርመኑ ንጉሥ ፣ በፖርቱጋሉ ንጉሥ ፣ ወዘተ በተደነገጉ ሕጎች መሠረት ( ኦርደርስ ኢንካውንስል ) ቅኝ ግዛቶችን የማስተዳደሩ የአሠራር ልምድ የባዕድ አገዛዝ በመጫኑ ምክንያት የተፈጠሩት ማህበራዊ ችግሮች ይበልጥ እንዲባባሱ አደረገ እንጂ ፣ የችግሮች መፍቻ ቁልፍ ሊሆን አልቻለም ። በእንዲህ ዓይነቶቹ ሕጎችና በቅኝ ግዛቶቹ ውስጥ ባለው ማህበራዊ ግንኙነቶች መካከል በጥልቀት እየሰፋ ለሄደው ልዩነት ሶስዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ምንም መልስ አልነበረውም ። ይልቁንስ ገሃድ ሊሆን የቻለው ሐቅ ፣ ኃይልን በመጠቀም የቅኝ ግዛትን ዓላማ ትክክለኛ ለማስገኘት የተደረገው ጥረት ሁሉ ፣ ቅኝ ገዥነት መሠረታዊ ዓላማው « የማሰልጠን ተልዕኮ » ሳይሆን ፣ እርቃኑን የቀረ የኢኮኖሚ ብዝበዛ መሆኑ ነበር ።

የሶስዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ዋነኛ ድክመት የመነጨው ራሱ ቲየሪው በራሱ ላይ ከጣለው ገደብ ነው ። ሕግ የማህበራዊ ክስተቶች ውጤት ብቻ ሳይሆን የማህበራዊ ሥርዓት መቀየሻ[23] መሳሪያ ነው የሚለውን የፓውንድን አስተሳሰብ በመከተል ፤ ሶስዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ሕግ በተለያዩ አዋጆች ላይ ያልተመሠረተ የጊዜውን ፍላጐት ብቻ የሚያንጸባርቅ የዳኝነት ቴክኒክ አድርጎ ቆጠረው ። ስለዚህም ፣ የሕጎችን መዋቅርና የማህበራዊ ግንኙነቶችን ሕጋዊ ቅርጾች በአግባቡ መተንተን ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም ሶስዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ ካደ ። በዚህ ፋንታ ፤ በግልጽ የሚታወቁ ሶስዮሎጂካዊ ጭብጦችን ከሕግ አንጻር በመተርጎም ብቻ ተወሰነ ። ሕግን በሚመለከት ፍጹም መካኒካል የሆነ አቋም በመውሰዱ የሶስዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ አገልግሎት ማህበራዊ ግንኙነቶችን እንደማይለወጡና ከዕድገትና እንቅስቃሴ ሐቲት ውጭ የሆኑ አድርጎ በሚቆጥረው ሊጋል « ሪያሊቲ » ወይም « አክቿሊቲ »[24] በመባል በሚታወቀው የኬልሰን አክራሪ የኖርማቲቪዝም ፍልስፍና በመተካት አከተመ ።

## መ/ ኒኦ—ናችራሊዝምና የካፒታሊስት ኢምፒሪያሊዝም ድምበር ዘለል ስትራተጂ

የሶስዮሎጂካል ጁሪስፕሩደንስ የተወሰኑ የሕግ ጥያቄዎችን ( ለምሳሌ የሕጋት አወቃቀርን ፣ የሕግ አተረጓጐምን ፣ የሕጎች አወጣጥን ወዘተ ) ለመፍታት የሚችል የሕግ ቲየሪ ለመሆን አለመብቃት ፣ እና ይበልጥ አጠቃላይ የሆኑ ቁሳዊ ፣ ፖለቲካዊና ሞራላዊ የሕግ መነሻ ምክንያቶችን ( ማለትም የሕጐችን ይዘት ወይም ውስጠ-ባህርዩን ለሚመለከቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት አለመቻል)፣ እንደዚሁም ለቅኝ አገዛዝ አስፈላጊነትና ለካፒታሊስት ሕጋዊነት ተጨባጭ ማረ

ጋገጫ ( ጀስቲፊኬሽን ) ለማቅረብ አለመቻሉ ፣ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የፍልስፍናና የርዕዮተ—ዓለም ክስረትን አስከተለ ።[25] ይህም ከታሪክ አኳያ ሲታይ ፣ ካፒታሊዝም በቀውጢ ዘመን ላይ መሆኑን — የመሞቻው ጊዜ መጀመሩን — አመለከተ ።

አጼያዊ ግዛቶች መፈረካከስ የጀመሩት በ20ኛው ምዕተ—ዓመት መጀመሪያ ላይ ከታላቁ የሩሲያ የጥቅምት አብዮት ማግሥት ጀምሮ ነው ። በ1940ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ላይ የካፒታሊዝም የርዕዮተ—ዓለም ክስረት ፣ የመፈረካከሱን ሂደት ይበልጥ አፋጠነው ። ይህም በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ጥልቀት እያገኘ መጥቶ ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት በሆነው ቅራኔ ተንጸባርቋል ። ይህን ተከትለው በቅኝ ግዛቶች ውስጥ ( ለምሳሌ በእስያና በአፍሪካ ) የተፋፋሙት ሕዝባዊ ንቅናቄዎችና የፖለቲካ ትግሎች ቅኝ ገዥዎች ሳይወዱ በግድ ለብዙዎቹ ቅኝ ግዛቶቻቸው የፖለቲካ ነፃነት እንዲሰጡ አስገደዷቸው ። በእነኝህ ሁኔታዎች ምክንያት « አዲስ » የሕግ ፍልስፍና የመፈለጉ ተግባርም ተካሄደ ። ይህም የካፒታሊዝምን የዘፈቀደ አሠራርና ሕገ—ወጥነት ፣ ቲየሪ ቀምሮ ለማሳየት ወደ ተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና መመለስ አስፈላጊ ነው ለሚለው ክርክር መንገድ ከፋች ሆነ ።

ያረጁና ያፈጁትን « የእኩልነት » ና « የነጻነት » ጽንሰ—ሃሳቦችን እንደገና በማንሳት ፣ ቦዴንሃይመር ሕግ « በሰው ተፈጥሮ » ላይ የተመሠረተ መሆኑንና እንዚህም ጽንሰ—ሃሳቦች በማንኛውም ሕጋዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን አበክሮ አስገነዘበ ።[26] ይሁን እንጂ ፣ በሕግ ከለላ ሥር በነበሩት የተወሰኑ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ውስጥ የተከሰተው በተጨባጭ ግንኙነቶችና በሕጋዊ እውነታ ( ሊጋል ሪያሊቲ ) መካከል ያለው ቅራኔ ፣ ቲየሪው ትክክለኛ አለመሆኑን ይጠቁማል ።

ፉለርም ባደረገው አስተዋጽኦ የሕግን ውስጣዊ ግብረ—ገብነት ( ኢነር ሞራሊቲ ) ፤ ማለትም ማንኛውም የሕግ ሥርዓት ሊያሟላው የሚገባው የመጨረሻ ዝቅተኛ መመዘኛ የሚሆኑ የሥነ—ምግባር ሥነ—ሥርዓት ደንቦችን ነደፈ ። እነዚህም መመዘኛዎች አጠቃላይነት ፣ የሕጎች በአዋጅ መልክ መውጣት ፣ የሕጎች ተፈፃሚነት ወደፊት ስለመሆኑ ፣ ማለትም ሕጎች በምንም ዓይነት ሁኔታ ወደኋላ ተመልሰው እንዳይፈጸሙ አጠቃላይ የሆነ ክልከላ ፣ ግልጽነት እና ለሰዎች በሚገባ ቋንቋ መዘጋጀት ፣ ሊፈጸሙ የማይችሉ ግዴታዎችን ማስወገድ ፣ ሕጎችን ቶሎ ቶሎ አለመለዋወጥ ፣ የታወጁ ሕጎችና የባለሥልጣን ድርጊቶች መጣጣማቸውን ማረጋገጥ ፣ ናቸው ። በፉለር አስተሳሰብ መሠረት ፣ እነዚህ መመዘኛዎች ሕግ ምላሽ ሊሰጣቸው በሚገባ የሰዎች ግንኙነቶች ላይ የተመሠረቱና በሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች መካከል አጸፋዊ ምላሽ (ሬሲፕሮሲቲ) እንዲኖር አስፈላጊ ናቸው ።[27]

በተጨባጭ የሰው ልጅ ግንኙነቶችና በሕሊናዊ አመለካከት ( ሞራሊቲ ) መካከል መተሳሰር መኖሩን ፣ ይህም ሕሊናዊ አመለካከት ( ሞራሊቲ ) በርዕዮተ—ዓለም መልክ እንደሚገለጽ ሐቁን በማመኑ ፣ የፉለር አስተሳሰብ ታዋቂነትን አትርፏል ። ይሁን እንጂ ፤ ቲየሪው በደንብ የዳበረ አይደለም ። ይህ ቲየሪ እንዴት እንደዳበረ ለማወቅ ከፈለግን የፉለር ሐያስያን የሰጡትን ትችቶች ማየት ይኖርብናል ። ይህን አመለካከት ከተቹት ብዙ ሐያስያን መካከል ፣ ለፉለር «የሥነ—ሥርዓት » ቲየሪ ለሰሚው ግራ በሆነ አኳኋን ነፍስ የዘራበትን ኻርትን ልንጠቅስ እንችላለን ። የኻርትን ትችት ለሰሚው ግራ የሚያደርገው እሱ የቀመረው የ«ሰብስታንቲቭ» ቲየሪ በሕግ እና መልካም ሥነ—ምግባር እንዲሟሉ በሚጠይቃቸው ሁኔታዎች መካከል ያለውን መተሳሰር የሚክድ ቢሆንም እንኳን ፣ የፉለር ቲየሪ ያለውን ጉድለት በማሟላት ስለሚደመድም ነው ።

በሕግና በመልካም ሥነ—ምግባር ( ሞራሊቲ ) መካከል ግልጽ ልዩነት አለ ፤ የሚለውን አስተያየት በማጥበቅ ፣ ኻርትና በርከት ያሉ ሌሎች የምዕራቡ ቡርዝዋ የሕግ ምሁራን ፣ አንዳንድ « ሕጋዊ » ድርጊቶች ከሞራል አንጻር የተሳሳቱ ሊሆኑ ይችላሉ ፤ የሚለውን ሃሳብ ስህተተኛነት ለማስረዳት ከፍተኛ ሙከራ አደረጉ ።[28] ይህም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ፤ ቅኝ ገዥነት ያለው ሞራላዊ መሠረት ምንድነው? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ በእንጭጩ ለመቅጨት የታቀደ ነበር ። ከፊል ሶስዮ ሎጂካዊ የሆነ አመለካከት በመያዝ ፤ ኻርት የሕጎችን ይዘት ከ« ተፈጥሮ ክስተቶች » ጋር አዛመደው ። በኻርት አስተሳሰብ መሠረት ፣ ሕጎች የተወሰነ ይዘት ( ስፐሲ ፊክ ኰንተንት ) እንዲኖራቸው የሚያስፈልግበትን ምክንያት የሚገልጹ ማንም የሚያውቃቸው አንዳንድ በጣም ግልጽ የሆኑ ሐቆች ( ሲምፕል ትሩይዝምስ ) አሉ ፤ ( እነኝህም ፤ ሰው በተፈጥሮው ለጥቃት የተጋለጠ መሆኑ፣እኩልነት ተቀ ራራቢ መሆኑ ፣ በጎ አድራጊነት ውሱን መሆኑ ፣ ጥሬ ዕቃዎች ( ሪሶርስስ ) ውሱን መሆናቸው ፤ እና የመግባባትና የፈቃደኝነት ጥንካሬ ( ስትሬንግዝ ኦቭ ዊል ) ውሱን መሆን ፣ ናቸው ) ።[29]

« የተፈጥሮ ሕግ እጅግ ዝቅተኛው ይዘት » የሆነው ይህ ይዘት ፣ ሰብአዊ ፍጡ ርን ፣ አካባቢያቸውንና ፣ ዓላማቸውን በሚመለከቱ እጅግ ተራ በሆኑ ሐቆች ላይ የተመሠረተና በማንም ዘንድ የሚታወቁትን የምግባር መመሪያዎች የሚያጠ ቃልል ነው ።[30] ይህም ማለት ፣ ለኻርት የሕጎች ሁሉ መሠረት « የተፈጥሮ ሕግ » ነው ፤ ማለትም ሰብአዊ ፍጡር በሕይወት እንዲኖር እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው ምክንያት « በተፈጥሮ በሕግ የተከለከሉ » ሰብአዊ ድርጊቶች ።[31] ይህም የሥነ —ምግባር እሴቶችን ( ሞራል ቫልዮስ ) በሥርቆሽ በር አስርጎ በማስገባት ከሕግ ጋር ለማዳቀል የተፈጥሮ ሕግ ይጠቀምበት የነበረው የጥንቱ ቴክኒክ ምሳሌ ነው ። « በተፈጥሮ የተከለከሉ የሰው ልጅ ድርጊቶች » እየተባሉ የሚነገርላቸው ድር ጊቶች የካፒታሊስቱን ሥርዓት የሚጻረሩ ድርጊቶች እንጂ ሌላ ሊሆኑ አይችሉ ምና ። ይህ የካፒታሊዝምን ትክክለኛነት ለማሳየት የሚደረገው ሙግት ስለሕግ የምናደርገውን ቲየሪያዊ ምርምር በካፒታሊስቱ የሕግ ሥርዓት « ሕጋዊ » ናቸው ተብለው በሚቆጠሩት ደንቦች ላይ እንድንወሰን ብቻ ሳይሆን ፣ « በተፈ ጥሮ ሕግ የተከለከሉትን » ( ማለትም የካፒታሊስቱን የሕግ ሥርዓት ) የሰብአዊ ፍጡር ድርጊቶች ( ለምሳሌ ፣ ቅኝ አገዛዝንና ሌሎች የካፒታሊስቶች ተግባሮችን) እንዳንቃወም ይከለክለናል ።

ሌላው በአሜሪካን ጁሪስፕሩደንስ ውስጥ የሚገኝ የዚህ ተጓዳኝ የሆነው የጊ ዜው ቲየሪ ፣ ሊበራል ስቴት የተሰኘው ነው ። የዚህም ቲየሪ ምንጩ « የተፈ ጥሮ ሕግ » ሲሆን ፣ ያዳበረውም ሎክ ነው ።[32] የቲየሪው ታዋቂ አቀንቃኞች የሆኑት ኻርትና ሳክስ ሕግን እንደ « ክንዋኔ ማስፈጸሚያ መዋቅር » ( ፋሲሊቴ ትቭ ፍሬምወርክ ) አድርገው በመቁጠር በሰፊው አብራሩት ። በዚህ መዋቅር ውስጥ ግለሰቡ እንዳሰኘው የግል ጥቅሙን ለማሳደድና ለደህንነቱ ይበጀኛል የሚለውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ነጻነት ይኖረዋል ።[33] የካፒታሊዝምን የ « ነጻ ንግድ »[34] ምስጢረ—ምጣኔ—ሀብት የሚያንጸባርቀው የዚህ ቲየሪ የሕግ ቀመር ፣ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በኅብረተሰብ ውስጥ እርስ በርስ የሚደጋገፉ መሆኑ ንና ለአንድ የሕግ ሥርዓት አስኳል የሆኑት መሠረታዊና ሥነ—ሥርዓታዊ « መግ ባባቶች » « አጠቃላይ ተቀባይነት » የማግኘታቸውን አስፈላጊነት አጉልቶ አሳየ ።[35]

ይህ ቲየሪ ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀጥተኛ አግባብነት ስላለው ሳይሆን፣(በዚህ ነጥብ ላይ ክርክር ሊቀርብበት የሚችል ቢሆንም )፣የዚህ ቲየሪ የሕግ—ቀመር

ወደ ከፍተኛ የጽንሰ—ሃሳብ መሳሪያነት ስለተሸጋገረና አሜሪካም በዓለም ላይ የበላይነቷን የሜነችው በዚህ ጽንሰ—ሃሳብ መሳሪያነት በመሆኑ ፣ ተለይቶ መጠቀስ የሚገባው ነው ። የዚህ ኢኮኖሚያዊ እድገት ዋና ምክንያት ፣ አሜሪካ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግ ውስጥ ከካፒታሊስቶቹ አገሮች ሁሉ በወታደራዊና በኢኮኖሚ መስክ እጅግ ኃያል መንግሥት ሆና ለመውጣት መቻሏ ነው ። ይህም አሜሪካ የተጎናጸፈችውን የበላይነት የበለጠ ለማጠናከር ያስቻላት የታሪክ ምዕራፍ የተከፈተበት የታሪክ ወቅት ነበር ። ይህን ዓላማዋን ከግብ ለማድረስም ሌሎች ተግባሮችን ከማከናወን በተጨማሪ ፣ ነጻ ኢኮኖሚያዊ ቀጣናዎችን በመላው ዓለም ዙርያ መዘርጋት ነበረባት ፤ ( ማለትም የአውሮፓን ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖል መሰባበር ) ፤ ቀጥሎም ፣ ( የአሜሪካን ኢምፐሪያሊዝም ባንዲራ አውለብላቢ ለሆኑት ) የአሜሪካ የግል ኮርፖሬሽኖች ፣ በአውሮፓ ካፒታሊስት መንግሥታት የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ገበያዎች ሽቀጣቸውን እንዲያራግፉ አመቺ ሁኔታ መፍጠር ነበረባት ።

እነዚህ ዓላማዎች ተግባራዊ የተደረጉበት ዋነኛ የሕግ መዋቅር ( ሊጋል ፍሬምወርክ ) የኢንተርናሽናል ሕግ ነው ። ጀሱፕ ፣ ፍሪድማን ፣ እና ማክዱጋልን በመሳሰሉ ቡርዣዋ የሕግ ምሁራን እየታገዘች ፣ ኢንተርናሽናል ሕግ በጣም እንዲሰፋና ሁለንተናዊ ዘርፍ ኖሮት በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር የሚገኙትን የኤሲያንና የአፍሪካን አገሮች እንዲያቅፍ የማድረጉን ተግባር አሜሪካ በግንባር ቀደምትነት መርታለች ፡ ለምሳሌም ፣ መደጋገፍ ( ኢንተርድፐንደንስ ) የሚባለው ጽንሰ—ሃሳብ « የዓለም መስተዳድር » ወይም « ኢንተርናሽናል መስተዳድር » በሚል ጽንሰ—ሃሳብ ተተክቶ ፣ በዓለም ላይ ያሉትን መንግሥታት ሁሉ እንዲያቅፍ ተደርጎ ፣ የኢንተርናሽናል ሕግ መርህ ወደሆነው « የመንግሥታት መደጋገፍ » መርህ ተለወጠ ።[26] ይህም የአዲሶቹን መንግሥታት ነጻነትና ሉዐላዊነት የሚያጠናክር መስሎ ታየ ። በተለይም አዲሶቹ መንግሥታት ከቀድሞ ቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር ብቻ ሳይሆን ፣ ከሌሎችም መንግሥታት ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን ለማድረግ ሕጋዊ እውቂያን አገኙ ። ይህም ሁኔታ እነኝህን መንግሥታት ለዓለም አቀፋዊ ብዝበዛ ( ዩኒቨርሳል ኤክስፕሎይቴሽን ) አጋለጣቸው ። የአሜሪካ ድንበር ዘለል ኮርፖሬሽኖች በእነኝህ የእጅ አዙር ገበያዎች ሸቀጣቸውን ለማራገፍ እንዲያስችላቸው በጀሱፕ የተቀመረው « ድምበር—የለሽ » ሕግ ( ትራንስናሽናል ሎ ) ጽንሰ—ሃሳብ ቀደም ሲል በፕራይቬትና በፓብሊክ ሕግ መካከል የነበረውን ልዩነት በመናድ ፣ የግል ኮርፖሬሽኖች በፓብሊክ ኢንተርናሽናል ሕግ ጥላ ሥር እንዲጠለሉ የሚያስችል የሕግ እውቂያ እንዲያገኙ በመሳሪያነት አገለገለ ።።[37]

ሌላው ወደ ኢንተርናሽናል ሕግ ጽንሰ—ሃሳብነት የተለወጠው የሊበራል ስቴት ቲየሪ ቅርንጫፍ ፣ «አጠቃላይ ተቀባይነት » (ጄነራል አክስፕታንስ) የተሰኘው መርህ ነው ። የዚህ መርህ ትርጉም ባጭሩ « በሕጉ መሠረት ውሳኔ የተሰጠባቸው » ጉዳዮች ሁሉ « በሕጉ መሠረት እስኪሻሩ » ድረስ ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል የሚል ነው ። በዚህ መርህ በመመርኮዝም የእስያና የአፍሪካ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች ወደ ዓለም ማህበራት በአባልነት ሲገቡ ፣ ብሔራዊ ጭቆናን ፣ የቅኝ ግዛት ዘረፋንና የኢምፐሪያሊስትን ውንብድና የሚያንጸባርቁና የሚያጠናክሩ ሕጎችን ጨምሮ ፣ ጠቅላላውን የኢንተርናሽናል ሕግ አሜን ብለው እንዲቀበሉ ተገደዱ ።[38] የዚህ መርህ በኢንተርናሽናል ሕግ በገቢር መተርጎም ፣ ኢንተርናሽናል ሕግ ይዘቱን ሳይለውጥ እንዲቆይ ለማድረግና ፣ የካፒታሊስቱን ዓለም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዓላማ ለማራመድ ጠቅሟል ።

## II. ኒኦ ኮሎኒያሊዝምና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ

### /ሀ/ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዓላማዎችና ዘዴዎች

ካፒታሊዝም የደረሰበት አጠቃላይ ቀውስ ካስገኛቸው መልካም ውጤቶች አንዱ የቅኝ አገዛዝ መፈራረስ መጀመሩ ነበር ። በ20ኛው ምዕተ—ዓመት መባቻ ላይ የተቀጣጠለው የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ፣ ኃይሉን በይበልጥ በማጠናከር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ቀንደኛዎቹ የካፒታሊስት መንግሥታት የዘረጉት የቅኝ አገዛዝ ጫና ድባቅ የሚመታበት ጊዜ መቃረቡን አበሰሩ ። እነዚህ ታሪካዊ ክንውኖች ( ደቡብ አፍሪካና ናሚቢያ ብቻ ሲቀሩ ) የቅኝ አገዛዝን የመጨረሻ ግብአተ መሬት አረጋገጡ ። የቅኝ አገዛዝ መውደቅም በቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶችና በቀድሞ ገዥዎቻቸው መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ጥያቄዎችን አስነሳ ። በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ምክንያት የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች በቅኝ ግዛቶቻቸው ላይ ሙሉ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት በነበራቸው ጊዜ ፣ ይገለገሉባቸው በነበሩት አሮጌ ዘዴዎች ብቁነት ሊተማመኑ አልቻሉም ። ስለዚህ ፣ ኢምፐሪያሊስት አገሮች ርካሽ ጉልበት ፣ የጥሬ ዕቃ ክምችት ፣ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰሻና የሸቀጥ ማራገፊያ ገበያ ፣ እንዲሁም ቅኝ አገዛዝ ፣ ያስገኛቸው የነበሩትን ሌሎች ጥቅሞች ሁሉ ሳይቋረጡ እንዲቀጥሉ ከፈለጉ ፣ የሆነ ግንኙነት የግድ መፍጠር ነበረባቸው ። ለዚህ ምላሽ ይሆን ዘንድ ፣ ኢምፒሪያሊስት አገሮች የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲያቸውን በመሸፈፋን ፣ አሮጌዎቹን ዘዴዎች በማሻሻልና አዳዲስ ዘዴዎችንም በመቀየስ ፣ እንዲሁም ስትራተጃቸውንና ታክቲካቸውን በመለወጥ ፣ ራሳቸውን ከአዲሶቹ ሁኔታዎች ጋራ አስማሙ ። በቀድሞ ቅኝ ግዛቶችና በኢምፒሪያሊስት ጌቶቻቸው መካከል የነበረው የዚህ ታሪካዊ ግንኙነት መለወጥ፣ ብዙ ዓይነት ዘዴዎች መቀየስንና ታክቲክ መቀያየርን አስከትሏል ። ይህም « የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ » ( ኒኦ—ኮሎኒያሊዝም ) በመባል ይታወቃል ። የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፣ « ኢምፒሪያሊስት መንግሥታት በረቀቁ ዘዴዎች ፣ በቀድሞ ቅኝ ግዛቶችና አሁንም ገና ነጻ ባልወጡ አገሮች ካፒታሊዝምን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ፣ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎችን ለመግታት ፣ የተቻላቸውን ያህል ትርፍ ለማጋበስና የኢምፒሪያሊዝምን ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ርዕዮተ—ዓለማዊና የወታደራዊ ስትራቴጂያዊ ይዞታ ለማጠናከር ፣ በተግባር ላይ ያዋሉት የካፒታሊዝም አጠቃላይ የሆነ የውድቀት ዘመን የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ነው » የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል ።[39] ከዚህ በላይ በተሰጠው ትርጉም መሠረት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዋና ዋና መለያ ጠባዮች ፣ ቁጥጥሩና ዘረፋው በግልጽ እንዳይታይ በሚያደርጉ አዳዲስ ዘዴዎች አማካይነት ፣ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶችን መቆጣጠር ፣ መጨቆን ፤ እና በረቀቁ ዘዴዎች ሀብታቸውን መዝረፍ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል ። ዘዴውና መልኩ የተለወጠ ይምሰል እንጂ ፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሠረታዊ ዓላማዎችና ግቦች ከቀድሞው ቀጥተኛ የሆነ ቅኝ አገዛዝ በምንም አይለዩም ።

የተፈጥሮ ሕግ ቲየሪዎች ዳግም ልደት የተከሰተው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ ወዲያውኑ እንደሆነ አሳይተናል ። ይህም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ከሆነ ቀውስ የደረሰበትና ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች ትግላቸውን ያፋፋሙበት ወቅት ነበር ። በ1960ዎቹ ዘመናት ፣ አፍሪካ ውስጥ ለሚገኙት ሲብዙዎቹ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶች ነጻነት መስጠትን ተከትሎ ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች ትግል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ፣ የተፈጥሮ ሕግ አስተሳሰቦችና ቲየሪዎች ዘርፋቸው እየሰፋ መምጣት ጀመረ ።[40] ስለዚህ የተፈጥሮ ሕግ ቲየሪ ዳግም ልደት ከቅኝ አገዛዝ መውደቅ ጋር አብሮ የተከሰተ ብቻም ሳይሆን ፣ የቅኝ አገዛዝ ውድ

ቀት ሂደት በገፋ መጠን የተፈጥሮ ሕግ ቲዮሪዎችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገው ጥረትም በዚያው ልክ ተጠናከረ ። እንግዲህ ፣ የተፈጥሮ ሕግ በቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶችና ገዥዎቻቸው በነበሩት አገሮች መካከል የተፈጠረውን አዲሱን ግንኙነት የሚገልጽ አንድ « አዲስ » የሕግ ፍልስፍና ለመቀመር አገልግሏል ። የዚህ « አዲስ » ፍልስፍና ታሪካዊ ሚናም ፣ ኢምፐሪያሊስት አገሮች ቅኝ ግዛት ያስገኝላቸው የነበረውን የማቴሪያል ጥቅም ሳያጡ ከአዲሶቹ ነጻ አገሮች ጋር « በሰላም አብረው የሚኖሩበትን » መንገድ ማዘጋጀት ነበር ። በተግባር ሲታይም ፣ ኒኦ ናችራሊዝም ካፒታሊስቶች የቅኝ አገዛዝን አስፈላጊነትና የካፒታሊዝምን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚጠቀሙበት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ርዕዮተ—ዓለማዊ መሳሪያ ነው ።

የተፈጥሮ ሕግ « የማይሸነፍ ጥንካሬ » ( ኦብስቲኔት ቫይታሊቲ ) ፣ « የማይሞት መንፈስ » ( እንዳይንግ ስፒሪት ) ፣ « ሁለንተናዊ ተግባራዊነት » እና « ፍጹምነት » መርሆዎች ፣ ወይም ደግሞ የሊጋል ፖዘቲቪዝምን ድክመት ብቻ በማስተጋባት የተፈጥሮ ሕግን ትንሳኤ ለማስረዳት የሚደረገው ሙከራ ሁሉ የሚያሳየው ነገር ቢኖር ፣ የኰሎኒያሊዝምን እውነተኛ ገጽታ ለመሸፋፈን የሚደረገውን የቡርዥዋ ጥረት ብቻ ነው ። ለካፒታሊስት የሕግ ሥርዓት ትክክለኛነት የተፈጥሮ ሕግ የሚያቀርበውን ማረጋገጫ ( ጀስቲፊኬሽን ) ከጠለቀ ምርመራና ትችት ለመከላከል ይህን ማድረጉ አስፈላጊ ነው ። በዚህም ምክንያት የቅኝ አገዛዝን « ፍትሐዊ » ሥርዓት ለመረዳት የምናደርገው ጥረት እንቀቅልሽ ይሆን ብናል ።[41] ይሁን እንጂ ፣ ሁለንተናዊነት ( ዩኒቨርሳሊዝም ) ፣ « ፍጹምነት » ( አብሶሊትዝም ) ፣ ፍትህ ፣ « ትክክለኛ አስተሳሰብ » ( ሪዝን ) ፣ « የተፈጥሮ ሕግ » እና « የተፈጥሮ መብቶች » በሚሉት ጽንሰ—ሃሳቦች ላይ በሚደረገው ማብራሪያ እንረካና ፣ እነኝህ ሁሉ ጽንሰ—ሃሳቦች የካፒታሊዝምን ሥርዓት የበላይነት በማህልም በዳርም ለማስከበር ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ግምጃ ቤት የሚፈልቁ የርዕዮተ—ዓለም መሳሪያዎች መሆናቸውን ለመገንዘብ ይሳነናል ።

በምዕራብ አገሮች ውስጥ ከፖዘቲቪዝም ወደ ኒኦ—ናችራሊዝም የተደረገውን ሽግግር በሚያስረዳው ጥናቱ ፣ ቱንኪን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን መሠረታዊ ባህርያት በግልጽ አስቀምጧቸዋል ። ቱንኪን እንደሚለው እነኝህ ኢምፐሪያሊስቶች በበላይነታቸው ላይ የተቃጣው የማይቀር ግብአተ—መሬት ጥቃት ሲያፋጥጣቸው የሀፍረት ማቅ ከመከናነብ ለመዳንና አንድም የትግሉን ማዕበል ለመገደብ ፣ አለበለዚያም የተሰነዘረባቸውን ምት ኃይሉን ለማብረድ ባደረጉት የደመ—ነፍስ ጥረት ፣ የቅኝ ግዛቶቹ መሠረት የተጣለበትን የሕግ መዋቅር፡—የእውነት መሠረቱ ኃይል ነው የሚለውን የ19ኛውን ምዕተ—ዓመት ሊጋል ፖዘቲቪዝም—እርግፍ አድርገው ተውት ። በምትኩም የኰሎኒያሊዝምን ሕጋዊ መሠረት—የለሽነት ለማሳየት የተፈጥሮ ሕግን ደንበኛ መሳሪያ አድርገው ተጠቀሙበት ።[42] ቱንኪን ሁኔታውን ሲያብራራ የቡርዠዋ የሕግ ሊቃውንት አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት የፖዘቲቭ ሎ እና በአጠቃላይም የኢንተርናሽናል ሕግ ሁሉ መሠረቱ የተፈጥሮ ሕግ ነው ብለው ሲያውጁ ፣ ኢምፒሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ተግባሩን ትክክለኛነት ለማሳየት ፣ ለተፈጥሮ ሕግ ከሚሰጠው ትርጉም ለየት ያለ ትርጉም ያላቸው መሆኑ ከታመነበት « ከሰው ተፈጥሮ » ፣ ከፍትህ አስተሳሰብና ፣ ከሌሎችም . . . የተወሰዱ ረቂቅ ( አብስትራክት ) መርሆችን እየጠቀሰ እንዲከራከር እድል ይሰጡታል ብሏል ።[43] ሽርዘንበርገርም ፣ « የተፈጥሮ ሕግ ቲዮሪዎች ዋና ሚና በፖዘቲቭ ሕግ አንጻር ሲገመገሙ ሕገ—ወጥ የሚሆኑ ተግባሮችን ትክክለኛ አስመስሎ ማሳየት ነው ፤[44] በማለት የቱንኪንን አባባል አጽድቆታል ።

/ ለ / በሊጋል አብስትራክሽን አማካይነት የካፒታሊዝምን ርዕዮተ—ዓለም ስለማራመድ

ይህን በቱንኪን የተገለጠውን ዓይነተኛ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘዴ ለማብራራት እስቲ የተፈጥሮ ሕግ ቲየሪን እንደ ሁለንተናዊ የሕግ ቲየሪ አድርጎ በማቅረብ ተወዳዳሪ ያልተገኘለትን የኻርትን አመለካከት በጥሞና እንመርምር ። የኻርት አመለካከቶች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ልዩ ልዩ ታክቲኮችና ሥውር ዘዴዎች ረቂቅ በሆኑ የሕግ ፈርጆች ( አብስትራክት ሊጋል ካቴጐሪስ ) በመሸፋፈን ፣ የኢምፒሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ይዘት ግልጽ እንዳይሆን በማድረግ የታወቁ ናቸው ። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ፣ የተፈጥሮ ሕግ ቲየሪን እንደፖዘቲቭ ሎ ለመቁጠር ፤ ኻርት የሚያደርገው የመሸፋፈን ጥረት ነው ። ኻርት የተጠቀመበት ዘዴና ፣ በመጠኑም ቢሆን ያገኘው የተሳካ ውጤት ፣ ከሌሎች የተፈጥሮ ሕግ የቡርዣዋ ሊቃውንት ሁሉ የመጠቀ ሊቀ—ሊቃውንት ያደርገታል ።

አንዳንዶቹን የተፈጥሮ ሕግ አቋሞች — የተፈጥሮ ሕግ ሊኖረው የሚገባ የመጨረሻው ዝቅተኛ ይዘት ( ዘ ሚኒመም ኮንተንት ኦቭ ናችራል ሎ ) — የሚቀበላቸው ቢሆንም እንኳን ፣ የሱ ቲየሪ ፣ ፖዘቲቪስት ቲየሪ መሆኑን ኻርት አበክሮ ያስገነዝባል ። « የተፈጥሮ ሕግ » ቲየሪን የሕግጋት ሁሉ መሠረት በማድረግ፣ ኻርት « ፍትህ » ፣ « ነጻነት » ፣ እና « እኩልነት » የተሰኙ የተፈጥሮ ሕግ ጽንሰ—ሃሳቦችን ኢስርጎ ለማስገባትና የፖዘቲቭ ሎ ዋነኛ ግብ ለማድረግ ችሏል ። እነዚህ ጽንሰ—ሃሳቦች ካላቸው ግልጽ የሆነ የሞራል ተቀባይነት እየታገዘ ፣ ኻርት « አዲሱ የካፒታሊስት ሥርዓት ለፍትህ ፣ ለነጻነትና ፣ ለእኩልነት የቆመ ነው ፤ የሚል የተሳሳተ አመለካከት እንዲፈጠር አድርጓል ። ይህም ሊክዱት በማይችሉትና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን በቀድሞ ቅኝ ግዛቶቻቸው ላይ ለተፈጸመው የጭቆና ፣ የሆረፋ ፣ የብዝበዛና የጭፍጨፋ ተግባር ፣ ኢምፒሪያሊስት አገሮች ከደሙ ንጹህ እንደሆኑ አድርጐ ለማቅረብ ከመሞከሩም በላይ ፣ « አዲሱ » የካፒታሊስት ሥርዓትም ፣ የቅኝ አገዛዝ ሕጋዊ መሠረት የለውም በማለት ደፍሮ እንዲናገር ረድቶታል ።

የቅኝ አገዛዝንና የካፒታሊስቱን የሕግ ሥርዓት ትክክለኛነት በነጠረ ሁኔታ ለማሳየት የተጠቀመበት ይህ ዘዴ ፣ ( የኻርት ቲየሪ ) « ሕጋዊ » ም ) ማለትም የፖዘቲቪስት ቲየሪ ) እንጂ « ሞራላዊ » ( ማለትም የተፈጥሮ ሕግ ቲየሪ ) ብቻ አለመሆኑን ለማስረዳት ኻርት ከፍተኛ ድካም እስኪደርስበት ድረስ ለፍቷል ። [45] የማረጋገጫነቱም መሠረት ፣ ይላል ኻርት ፣ ሕግ ሙታየት ያለበት እንደ « ሥርዓት » ማስከበሪያ ( ኦርደር ሲምፒሊሲተር ) ስለሆነ ከሞራል መለየት አለበት ። [46] ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው ፣ እንዲህ ዓይነቱ ክርክር የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ፣ ፀለሕግ የሚደረጉ የንድፈ—ሃሳብ ምርምሮች ሁሉ « አዲሱ » የካፒታሊስት ሥርዓት « ሕጋዊ » ናቸው በሚላቸው ሁኔታዎች ዙርያ ብቻ መወሰን እንዳለባቸው ነው ። በሕግና በሞራል መካከል የተፈጠረው ይህ የወሰን ክልል ፣ የቅኝ አገዛዝን የጭካኔ ድርጊቶች እንደወንጀልና ሕገ—ወጥ ተግባር ልንቆጥር ቀርቶ ፣ ከነሱ ጋር የተያያዙ ጭብጦችን እንኳን አንሥተን እንዳንወያይ ያደርገናል ። ምክንያቱም ፣ እነዚህ ድርጊቶች የሕግ ትርጉም አልነበራቸውም ፤ ገናም አልተሰጣቸውም ። [47] በመሆኑም ፣ ቢበዛ ቢበዛ ፣ ሕጉ ጉዳዬ የማይላቸው የሞራል ጥያቄዎች እንደሆኑ ይቆራሉ ማለት ነው ። የሆነው ሆኖ ፣ ሕግ ለፍትሕ ይቆማል ፤ በሚለውና ፣ ሕግ ስለነዚህ የጭካኔ ተግባራት ደንታም የለው ፤ በሚሉት

ሀሳቦች መካከል ስላለው ቅራኔስ ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ፣ ለተቃርኖው የሚጠየቅ
በት « አዲሱ » የካፒታሊስት ሥርዓት አይሆንም ። ሕግ ከሞራል መለየት ይገ
ባዋል የሚለው አባባል ፣ ከሕግ ቲየሪ መሠረታዊ መርህ የመነጨ ነው ።[48] በዚህ
የረቀቀ ዘዴያቸው አማካይነት ኻርትና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት በሆኑት አገሮች
ውስጥ የሚገኙት ደቀመዝሙሮቹ ፣ አሳፋሪውን የቅኝ ግዛት ምዕራፍ ለመዝጋ
ትና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አማካይነት ለካፒታሊዝም የእድሜ ልክ የአሳብ
መብት ሊሰጡት ተጣጣሩ ።

ይህ የካፒታሊስቱን ሕጋዊነት ለማሳመን የተቀየሰው ዘዴ ፣ ኻርት መሠረ
ታዊ የቲየሪ ጥያቄዎች የሚላቸውን ጥያቄዎች አስነስቷል ። ከጥያቄዎቹም መካ
ከል (1) የሕግና የሞራሊቲ መለያ መስከያው ምንድነው ? (2) ሕጋዊ ድርጊት
ከሞራላዊ ድርጊት በምን ይለያል ? የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው ። ለነዚህ ጥያቄዎች
የሚሰጡት መልሶች ከካፒታሊዝም ጋር በቅርብ የተሳሰሩ መሆናቸውን በአን
ክሮ ማየት ይገባል ። ምክንያቱም እነዚህ መልሶች ለቅኝ አገዛዝ የትክክለኛነት
ማረጋገጫ የተመረጠውን ዘዴ ሕጋዊ መሠረት የሚወስኑ ብቻ ሳይሆን ፣ ለ « አዲሱ
የካፒታሊስት ሥርዓትም የሕጋዊነት ማረጋገጫ የሚሆነውን ስለሚወስኑ ጭምር
ነው ። በተጨማሪም ፣ የራሱ የኻርት ቲየሪ ትክክለኛነትና የተፈጥሮ ሕግ ሁለ
ንተናዊ የሕግ ቲየሪ ለመሆን ብቁ የመሆኑ መሠረታዊ ጥያቄ ለነዚህ ሁለት ጥያ
ቄዎች በሚሰጡት መልሶች ይወሰናሉ ።

ለጥያቄዎቹ መልስ ሲሰጥ ፣ ኻርት የቲየሪውን ርዕዮተ—ዓለማዊ ይዘት ለመ
ደበቅ ሲል ፣ ሊጨበጡ በማይችሉ ረቂቅ ሃሳቦችና ግልጽ ባልሆኑ ቲየሪያዊ ቀመ
ሮች ይጠቀማል ። ውጤቱም ገሃዱን ሐቅ ረቂቅ ምስጢር ከማድረግ በቀር ምንም
እርባና የሌለው ፣ እርስ በርስ የሚቃረን ተራ አርባል ከመሆን አላለፈም ። ኻርት
እንደሚለው ሕግን ለመወሰንና « ሕጋዊውን » ድርጊት « ከሞራል » ድርጊት
ለመለየት የሚያገለግለው መመዘኛ « የእውቀያ መስጫ ደንብ » ( ሩልኦቭ
ሪኮግኒሽን) ነው ። እንደኻርት አባባል ይህ ደንብ የሥነ ምግባር ደንቦችንና የአ
ንድን ሥርዓት ሕግ ሌሎች « ሕጋዊ » ደንቦች ሁሉ መሉ በሙሉ ለመለየት የሚ
ጠቅም መመዘኛ ነው ።[49] ይህም ማለት ፣ « ሕጋዊ » ደንቦቹ ቀጥ ምውኑ ሕጋ
ዊነታቸውን ያገኙ ስለሆነ ፣ የ « እውቂያው መስጫ » ደንብ (ዘሩልኦቭ ሪኮግን
ሽን ) እነርሱኑ ለይቶ ለመገንዘብ ብቻ ይረዳናል ማለት ነው ። ሕጋዊነትን ግን
አያጎናጽፋቸውም ፤ በመሆኑም ሕጋዊነታቸወን ለማረጋገጥ መመ፤ኛ ሊሆን አይ
ችልም ። ይሁን እንጂ ፣ ኻርት ሊገለጽና ሊብራራ የማይችል ሎጂክ በመጠቀም
የሕግ ደንቦች ሕጋዊነታቸውን (ሊጋል ቫሊዲቲ) የሚያገኙት ከ « እውቂያ መስጫ»
ደንብ ነው ብለን እንድናምንለት ይፈልጋል ።[50] ኻርት ሊያሳምነን እንደሚጥ
ረው የሕግ ደንቦች ሕጋዊነት የሚመነጨው ከ « እውቂያ መስጫ » ደንብ ነው
የሚል ግምት ብንወስድ እንኳን ፣ « የእውቂያ መስጫ » ደንብ የሥርዓተ—ሕጉን
ደንቦች እንዴት አድርጐ ነው ሕጋዊ የሚያደርጋቸው ? የዚህስ የሕጋዊነት ማረ
ጋገጫ ደንብ ምንጭ ምንድነው ?

የመጀመሪያውን ጥያቄ በሚመለከት ኻርት መልስ ሊሰጥ ቀርቶ ሃሳብ እንኳን
አይጠቁምም ። የኋለኛውን በሚመለከትም ግልጽ ያልሆነና የማይጣጣም መልስ
ለመስጠት ይሞክራል ። « የእውቂያ መስጫ ደንብን » ሕጋዊ መሆን ወይም አለ
መሆን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሊነሳ አይችልም ፣ የሚል አቋም በመ
ያዝ ፣ ደንቡ ለአገልግሎት ተገቢነት ስላለው ብቻ በቀላሉ ተቀባይነትን ያገኛል ፤
በማለት ኻርት ሙጭጭ አለ ።[51] ታዲያ ተቀባይነት ማግኘት ብቻ ደንቡን ሕጋዊ
( ትክክል ) ያደረገዋል ማለት ነውን ? የእውቂያ መስጫ ደንብ በራሱ ይኖራል

የሚለው አባባል ፣ ሊሆን የሚችለው ባዕድ የሆነን ሐቅ መግለጫ ( ኤክስተርናል ስቴትመንት ኦቭ ፋክት ) ብቻ ነው ፣ በማለት ኻርት በአንድ ወቅት ተናግሯል ። የደንቡ አገልግሎትም « በአንድ በተጠቆመ ደንብ መሠረት እንደቡድን ደንብ ሆኖ ሙሉ በሙሉም ተቀባይነት ማግኘቱን የሚጠቁም አንዳንድ ገጽታን ( ፊቸር ) ወይም ገጽታዎችን ( ፊቸርስ ) » ለመለያ የሚያገለግል መሆኑን አምኖ ተቀብሏል ።[52] « ገጽታ ወይም ገጽታዎች » ምን ማለት እንደሆነ አሁንም ወዲያውኑ አልተብራራም ። በመጨረሻም ፣ እነኝህ ነጥቦች ፣ ምንጩ እንቆቅልሽ የሆነው የ « እውቂያ መስጫ ደንብ » ( ሩል ኦቭ ሪኰግንሽን ) መብራራት ያለባቸው ነገሮች መሆናቸውን ኻርት አምኖ ቢቀበለውም ፣ ግልጽ የሆነ መልስ ሳይሰጥ ያቆማል ። ይህ የሚያስረዳን ነገር ቢኖር ፣ «የእውቂያ መስጫ ደንቡ» (ዘ ሩል ኦቭ ሪኰግንሽን ) ውስብስብ ፣ ነገር ግን ፍ/ቤቶች ፣ ባለሥልጣኖችና ፣ ግለሰቦች አንዳንድ መመዘኛዎችን እየተጠቀሙ ሕጉን ለማወቅ የሚጠቀሙበት የተለመደ አሠራር ሆኖ የሚኖር መሆኑን ብቻ ነው ።[53]

ይህ ግልጽ ያልሆነና ነጥቡን በመሸሽ የተደረገ ማብራሪያ ፣ መጀመሪያ ወደ ተነሳንበት ጉዳይ ይመልሰናል ። ምክንያቱም ፣ ይህ ሕግን «ለይቶ ለማወቅ» ይረዳል የተባለው ልዩ መመዘኛ ፣ ምን እንደሆነ ማወቅ ስላለብን ነው ። የሆነ ሆኖ ፣ በሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ « ባለሥልጣኖች » ምግባር ( ቢሄቪየር ) ፣ « የእውቂያ መስጫ ደንብ » መኖርን ይወስናል ፤ የሚለውን የኻርትን አመለካከት ብንቀበልም እንኳን ፣ « ሕጋዊ » የሆነው ነገር « አዲሱ » የካፒታሊስት ሥርዓት « ሕጋዊ » ነው የሚለው ፣ ወይም ኻርት እራሱ ምስጢራዊ በሆነ አነጋገር ( ሚስትካሊ ) « ውስጣዊ የሕግ መመሪያ » ( ኢንተርናል ስቴትመንት ኦቭ ሎ ) ብሎ የሚጠራው ነው የሚለውን አቋማችንን አሁንም ያረጋግጥልናል ። « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ን ምንነት ለመደበቅ ኻርት ያደረገውን የረቀቀ ጥረት ፣ ራዝ የኻርት ጥረት የ « እውቂያ መስጫ ደንብ » የልማድ የሕግ ደንብ ነው ፤ መሠረቱም ልማዳዊ አሠራር ነው ፤ የሚለውን ነጥብ ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ ነው በማለት ገልጾታል ።[54] ኻርት ይህ ነጥብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለምን ጥረት አደረገ ብለን እንጠይቅ ይሆናል ። ለዚህ ጥያቄ ራዝ መልስ ለመስጠት ይሞክራል ። ግን የራዝ መልስም ቢሆን በሎጅክ አለመጣጣም ትችት ላይ ብቻ ከማትኮር በቀር ርቆ አልሄደም ። ይሁን እንጂ ፣ ጉዳዩ በጥልቀት ቢመረመር ፣ የኻርት ቲየሪ ለካፒታሊዝም የሕግ ባህል የበላይነት መሠረት ለመጣል ያደረገውን የመሸፋፈን ጥረትና የቲየሪውን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ገጽታ ( ኒኦ ኰሎኒያል ካራክተር ) ያሳያል ።

የኻርት ቲየሪ መሠረታዊ መነሻ ነጥብ ፣ ታሪካዊ መሠረት በሌለው ሁኔታ ፣ እንዲሁ ዝም ብሎ ኅብረተሰብን በ « ቅድመ—ሕግ » እና በ« ሕግ » ማህበራዊ መዋቅሮች መከፋፈል እንደሆነ ይታወሳል ። በእርግጥ ፣ እንደተለመደው ፣ ለዚህ ክፍፍል መሠረት የሆኑ ምክንያቶች አልተሰጡም ። አንዱን ኅብረተሰብ « የሕግ » ፣ ሌላውን « የቅድመ—ሕግ » ስለሚያደርገው ምክንያትም ሆነ ፣ ኅብረተሰብ ከአንዱ ዓይነት ወደሌላው ስለሚለወጥበት ሁኔታ ምንም የተነገረን ነገር የለም ። ኻርት የሚነግረን ነገር ቢኖር ፣ « የቅድመ—ሕግ » ኅብረተሰብ የሚባሉት ፣ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው በሚያስገነዝቡ ቀላል የልማድ ደንቦች ላይ በተመሠረተ መዋቅር የተዋቀሩ መሆናቸውን ነው ። የንዲህ ዓይነቱ ማህበረሰብ መዋቅር ደንቦች ፣ ሕግ ለመባል የሚያስችሏቸው ባህርያት ስለሚጎድሏቸው ፣ « የመጀመሪያ ደረጃ የግዴታ ደንቦች » ( ፕራይመሪ ሩልስ ኦቭ ኦብሊጌሽን) ተብለው ይመደባሉ ። እንደኻርት አባባል ፣ እነዚህ የማህበረሰብ መዋቅሮች የሚገኙት « በጥንታዊ » ( ፕሪሚቲቭ ) ኅብረተሰቦች ዘንድ ብቻ ነው ። ( ኻርት

ጥንታዊ ኅብረተሰቦች የሚላቸው ቅድመ—ቅኝ ግዛትና ቅኝ ግዛት የሆኑ ኅብረተሰቦችን ነው ) ። [55] « የሕግ » ኅብረተሰቦች ግን ፣ « ከመጀመሪያ ደረጃ የግዴታ ሕጎች « በተጨማሪ « የሁለተኛ ደረጃ ደንቦች » ( ሰከንደሪ ሩልስ ) የሚባሉ የዳበሩ ደንቦች አሏቸው ። በነኝህ « ሁለተኛ ደረጃ ደንቦች » ውስጥም ፣ የሕግ አውጭውንና ሌሎች ፍርድ የሚሰጡና ደንብ የሚያስፈጽሙ ተቋሞችን የሚያቋቁሙ የሥልጣን ማቀዳጃ የሁለተኛ ደረጃ ደንቦች አሉ ። [56] የ « ሁለተኛ ደረጃ ደንቦች » ከ « መጀመሪያ ደረጃ ደንቦች » ጋራ ተዳምረው ሕግን ይመሠርታሉ ። [57] ይህ በደንብ ሊተኮርበት የሚገባ ነጥብ ነው ። « የሁለተኛ ደረጃ ደንቦች » ሊኖሩ የሚችሉት በከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ኅብረሰተቦች ዘንድ ነው ፤(ይህ አባባል ኢምፔሪያሊስት አገሮችን እንደሚያመለክት ለማንም ግልጽ ነው ) ። [58]

እንግዲህ በኻርት ጁሪስፕሩደንሻል መመዘኛ መሠረት ፣ ሕግ ማለት የመጀመሪያ ደረጃ ደንቦችና የሁለተኛ ደረጃ ደንቦች ስብሰብ ነው ። ይህም በመሠረቱ በሕግና በሞራል ደንብ መካከል ያለው ልዩነት ፣ ደንቡ የተገኘበትን ኅብረተሰብ ዓይነት የሚያመለክትና ፣ የኻርትን ቲየሪ ርዕዮተ—ዓለማዊ ይዘት የሚያሳይ ነው ማለት ነው ። ከሕግ ቲየሪ አንፃር ሲገመገም ፣ ይህ መመዘኛ ( ክራይተሪየን ) በጣም አስቂኝ ከመሆኑም በላይ ፣ የሕግ ቲየሪ ጠቅላላ መሠረት የተፈጥሮ ሕግ ነው ፤ የሚለውን ክርክር ክስረት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ። ይሁን እንጂ ፣ ይህ መመዘኛ አስቂኝና ፋይዳቢስ ቢሆንም ቅሉ ፣ በኻርት ቲየሪ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ ፣ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም ።

በመጀመሪያ ደረጃ ቲየሪዮ ፖዘቲቭስት ነው ፤ በማለት ኻርት መላውን ዓለም ለማሳሳት የሚጠቀምበት ስትራተጂያዊ የጽንሰ—ሃሳብ መሳሪያው ነው ። በሌላ አነጋገር ፣ የቲየሪውን ሕጋዊ መሠረት ለማጽናትና የቅኝ አገዛዝንና የካፒታሊዝምን የሕግ ሥርዓት ትክክለኛነት ለማሳየት የማያስችል ወሳኝ የጽንሰ—ሃሳብ መሳሪያው ነው ። በሁለተኛ ደረጃ ፣ ይህ ደግሞ የበለጠ ጠቃሚነት አለው ። ይህ መመዘኛ ኻርት « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ( ሩልስ ኦቭ ሪከግኒሽን ) የልማድ ሕግ ደንብ ተብሎ እንዳይጠራ ለምን አጥብቆ እንደተቃወመ ፍንጭ ይሰጠናል ። ይህ ፍንጭም የኻርት ቲየሪ ይዘት ምስጢር የሚገለጥበትን ቁልፍ ይዟል ።

ኻርት ራሱ ከሚያቀርበው ትንታኔ እንደምንገነዘበው ፣ « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ማለት የሥልጣን ማቀዳጃ ሁለተኛ ደረጃ ደንብ ማለት ነው ። ስለዚህ ፣ ሊኖር የሚችለውም በ « ሕግ » ኅብረተሰቦች ( ሊጋል ሶሳይቲስ ) ዘንድ ብቻ ነው ። አለበለዚያ በ « ቅድመ—ሕግ » ኅብረተሰቦች ( ፕሪ ሊጋል ሶሳይቲስ ) ዘንድም ሊኖር ይችላል ብሎ ማለት ፣ እራሱን በራስ መቃረን ይሆናል ። ስለዚህ ፣ እርስ በርሳቸው የሚጣጣሙ ሃሳቦችን የማቅረቡ ሎጅክ አስፈላጊነት ፣ ኻርት ገሃዱን እውነት እንዳይቀበል አግዶት ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ፣ የኻርት ቲየሪ ይዘት ፣ ከገሃድ እውነታ ጋር መጣጣም አልነበረም ፤ ሐቅ የሚጎድለው ቢሆንም እንኳን ፣ የ « እውቂያ መስጫ ደንብ » የ « ሕግ » ኅብረተሰቦች ብቻ እንዲሆን የሚያስገድድ በአውሮፓ ላይ ያተኮረ ግልጽ የሆነ የርዕዮተ—ዓለም መጠበብም ነበረበት ።

ይህን ርዕዮተ—ዓለማዊ ግብ ለመቀዳጀት ሲባል ፣ የኻርት ቲየሪ ጥንታዊኅብረተሰቦች የሥልጣን መቀዳጃ ደንብ የላቸውም ለማለት የተገደደ መሆኑን መገንዘብ ይገባል ። ምክንያቱንም ሲገልጽ ፣ ኻርት « የነዚህ ኅብረተሰቦች ደንቦች በጣም ጥንታዊ ( ኋላ ቀር ) ከመሆናቸው የተነሳ ፣ ሕግ ሊባሉ አይችሉም » ይላል ። ስለዚህም ፣ « የመጀመሪያ ደረጃ የግዴታ ደንቦች » ፣ ወይም እንዲሁ የልማድ

ደንቦች ሊባሉ ይችላሉ ። « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ማለት የልማድ ሕግ ደንብ ነው ብሎ ኻርት ቢቀበል ኖሮ ፤ ጥንታዊ ለሆኑት የቅኝ ግዛትና የቅድመ—ቅኝ ግዛት ኅብረተሰቦች የካፒታሊዝምን ሕጋዊነት ሊዋጉበት የሚያስችላቸውን የሕግ ሥልጣን መስጠቱ እንደነበር መገመት አያዳግትም ። በመሆኑም ፣ « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ን የሥልጣን መቀዳጃ ለሆነው ለሁለተኛ ደረጃ ሕግ ብቻ መወሰኑና ከ « ጥንታዊ ኅብረተሰቦች » ጋር አለማያያዙ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው ። ዋናው ምክንያት ይህ ነበር ( ይህ ደግሞ የኻርትን ቲየሪ መሠረታዊ ይዘት ያብራራል ) ኻርት የ « እውቂያ መስጫ ደንብ » ን የልማድ ሕግ ደንብ ነው ብሎ ሊጠራው ያልፈለገው ። ምክንያቱም « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ሊሆን የሚችለው የ « ሕግ » ደንብ ነው ፤ በማለት ኻርት እንደምንም ብሎ « ኦዲሱን » የካፒታሊስት ሥርዓት የበላይነትና ደህንነት ጠብቋል ። ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝም ሕጋዊ ዋስትና ሰጥቷል ።

## ሐ/ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝና በኒኦ—ናችራሊዝም መካከል ስላለው ዝምድና

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ስላለው የሕግ አፈጣጠርና በተግባር አተረጓጎም ሁኔታ ፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ስላለው የአስማሚነት ሚና የተደረገው ትንተና ( አናሊሲስ ) ምዕራባውያን የሕግ ሊቃውንትና ፈላስፋዎች አውቀው እንደፈጠሩት ነገር ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት ማስገንዘቡ ተገቢ ነው ። በተቃራኒው ፣ በምሁራን እና ቁሳዊ ምርት ( ኢንተለክቹዋል ኤንድ ማቴሪያል ፕሮዳክሽን ) መካከል ካለው ነባራዊ ግንኙነት እንደመነጩ ተደርጎ መታየት ይኖርበታል ። [59] ይህም ማለት ፣ በልዩ ልዩ የሕግ ሊቃውንት የሚገለፁ አስተሳሰቦች ፣ ጽንሰ—ሃሳቦችና ቲየሪዎች የካፒታሊስቱ ሥርዓት ነባራዊ ፍላጎቶች ውጤቶችና የካፒታሊስቱን የምርት ግንኙነት የሚያንጸባርቁ ናቸው ።

አብዛኛውን ጊዜ እነዚሀ ግንኙነቶች በኅብረተሰቡ የገዥ መደቦች አመለካከቶች ይገለጻሉ ። [60] ነገር ግን ፣ ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው የሥራ ክፍፍል መሠረት እነዚህን ሃሳቦች የሚያፈልቁት የሕግ ሊቃውንት ናቸው። በመሆኑም ፣ የሕግ ሊቃውንቱ ረቂቅ ሃሳቦች ( አብስትራክት አይዲያስ ) ወይም « አይዲያል ፎርሙላ » በመጠቀም ለገዥው መደብ አስተሳሰቦች የሁለንተናዊነት ጠባይ በመስጠት እንደብቸኛና ፍጹማዊ ትክክለኛ ሃሳብ አድርገው ያቀርቧቸዋል ። በተጨባጭ ሲታይ ግን ፣ በነዚህ ሊቃውንት የሚፈልቁት ሃሳቦች ፣ ጽንሰ—ሃሳቦችና ፣ ቲየሪዎች ፣ በጊዜው ጎልቶ የሚታየው ቁሳዊ ግንኙነት መግለጫ ከመሆን አያልፉም ። ስለዚህ ፣ በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ የበላይነትን ባገኙ የሕግ ቲየሪዎች የሚገለጹት ሃሳቦች ሁሉ ፣ የካፒታሊስቱን የምርት ግንኙነትና የካፒታልን የበላይነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ። በዚህም ዓይነት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ከምሁራን የሚፈልቁት ሃሳቦች ሁሉ በተጨባጭ ከካፒታሊስቱ ሥልተ—ምርት ጋር ይዛመዳሉ ።

በመሆኑም በኒኦ—ናችራሊዝም የተገለጸው ፍትህ ፣ ነጻነት ፣ እኩልነት ፣ ሰብአዊ መብቶች ፣ ወዘተ ፣ የሚሉት ሃሳቦች ሁሉ ፤ በካፒታሊስቱ ማህበራዊ ግንኙነት ላይ የሚመሠረቱ ፣ የሚወሰኑና ፣ የሚቀየሱም ብቻ ሳይሆኑ ፣ የካፒታሊስቱን ሥርዓት ኅላማም ተግባራዊ ለማድረግ የታቀዱ ናቸው ። ለምሳሌም ፣ የቅኝ አገዛዝ የጭካኔ ድርጊቶች ለምን እንደወንጀል እንዳልተቆጠሩ ከዚህ ለመረዳት ይቻላል ። ምክንያቱም በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ እንደወንጀል የሚቆጠሩ ሁኔታዎች የሥርዓቱን ጥቅም የሚጻረሩ ብቻ ናቸው ። [61] የተፈጥሮ ሕግ ሊቃው

ንትና ኒኦ—ናችራሊስቶች ስለፍትህ ፣ ስለሕግ የበላይነት ( ሩል ኦቭ ሎ ) ፣ እኩል ነትን የሚያረጋግጥ የሕግ ሥርዓት ስለመመሥረት ፣ ስለነጻነት ፣ ወዘተ ሲናገሩ ፣ ስለማን ነጻነት ፣ እኩልነት ፣ መብት ፣ ወዘተ እንደሚናገሩ መመርመር አግባብም ፣ ግድም ይሆናል ።

እስካሁን ባቀረብነው ትንታኔ መሠረት ፣ መልሱ በኢምፒሪያሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙ ገዥ መደቦችና እያወቁ ከኢምፒሪሊያዝምና ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ጋር የሚተባበሩ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶችውስጥ የሚገኙ በዝባዥ መደቦች ፍትሕ እኩልነትና መብት ነው ። እነዚህ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች ውስጥ የሚገኙ በዝባዥ መደቦች ህልውናቸው በመጤ ካፒታል ላይ የተመሠረተና ያለርሱ ሊኖሩ የማይችሉ ናቸው። በእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች ውስጥ የውጭ ካፒታል የበላይነት ሊያገኝ የቻለው የአቀባባይ ከበርቴዎች ህልውና በውጭ ካፒታል ላይ የተመሠረተ በመሆኑና በአቀባባይ ከበርቴዎችና በውጭ ካፒታል መካከል የጠበቀ መተባበር ስላለ ነው ። ይህም የካፒታል የበላይነት ዋና ዋና በሆኑት የላዕላይ መዋቅር ተቋሞች የተደገፈ ነው። ከነዚህ ተቋሞች ውስጥ በወግ አጥባቂ ምሁራን ቁጥጥር ሥር የሚገኙና የሚሠሩ ት/ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ይገኙባቸዋል። የነዚህ ወግ አጥባቂ ምሁራን ድርጊት ከሚያገለግሏቸው ወይም ከሚመሳጠሯቸው መደቦች ፍላጎት ጋራ የተቆራኘና እስከተወሰነ ደረጃም በነዚሁ መደቦች የሚወሰን ነው ። ይህ በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሚጣልለት ጉርሻ የተገዛው «የምሁራን»[62] ቡድን ፣ የካፒታሊዝምና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ርዕዮተ—ዓለማዊ ዕድሜ እንዲራዘም ፣ ለምዕራቡ ዓለም ሃሳብ ፣ ጽንሰ—ሃሳብና ቲየሪ ታማኝ አገልጋይ በመሆን በቀጥታ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ከሚገኙ በዝባዥ መደቦች ጋራ ይተባበራል ።[63] እንግዲህ ፣ ኒኦ—ናችራሊዝም ከቅኝ አገዛዝና ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ታሪክ ጋር በቅርብ የተዛመደ መሆኑን በግልጽ የሚያሳየን ይህ ሐቅ ነው ፤ የፊተኛው ለኋለኛው ትክክለኛነት ሕጋዊና ርዕዮተ—ዓለማዊ ማረጋገጫ በመስጠት ።

## መ ደ ም ደ ሚ ያ

በምዕራቡ ካፒታሊስት አገሮችና በቅርቡ ነጻ በወጡ የአፍሪካ አገሮች ዋነኛው የሕግ ፍልስፍና ከጊዜ ወደጊዜ በተፈጥሮ የሕግ ፍልስፍና አንጻር እየተቀረጸና እየተዋጠ በመሄድ ላይ ነው ። ብዙ ምዕራባውያን የሕግ ሊቃውንት የተፈጥሮን ሕግ ፍልስፍና በመካብ ፣ ለፍልስፍናው ዳግም ልደት ዋና ምክንያት የራሱ የፍልስፍናው ውስጣዊ ባህርይ ነው በማለት ነገሩን አለባብሰው ለማለፍ ጥረዋል ። እነርሱ የሚያቀርቧቸው ማብራሪያዎች ግልብና በእውነት ላይ ያልተመሠረቱ መሆናቸውን በማስረዳት ለተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ማንሰራራት ዋናው ምክንያት ምን እንደሆነና ያስከተለውን ሁኔታ ለመተንተን ሲባል ፣ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የካፒታሊስቱን ዓለም ማህበራዊ ግንኙነቶች ማህበራዊ ይዘት በጥልቀት ለመመርመር ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ።

ትንታኔያችን እንደሚያመለክተው የካፒታሊዝም አጼያዊ የቅኝ አገዛዝ ከተንኰታኰተ በኋላ ፣ ምንም እንኳን የኢምፒሪያሊዝም የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ መሠረታዊ ይዘት ሳይለወጥ ቢቆይ ፣ በቀድሞ ቅኝ ግዛቶችና በኢምፒሪያሊስት አገሮች መካከል ለተፈጠረው አዲስ ሁኔታ እንዲያመች ፖሊሲውን ሸፋፍኖ ማቅረብ የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ነበረ ። ይህም የቀድሞውን የባርነት አገዛዝና የተቀነባበረ ዘረፋ ለመሸፋፈን ሲባል የቅኝ አገዛዝን አሮጌ ዘዴዎች መለዋወ

ጥና አዳዲስ ስትራተጂዎችና ታክቲኮችን መቀየስን አስከተለ ። ለዘመናዊ ካፒታሊዝም አዳዲስ ዘዴዎችን የመቀየሱ ተግባር ለ « አዲሱ » ካፒታሊዝም ዘመን— ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ጥርጊያ መንገድ ከፍቷል ። የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ዘዴዎች ዋነኛው የኢንዱስትሪና የፋይናንስ ካፒታልን ወደሌሎች አገሮች የሚያስገባባቸው ልዩ ልዩ ዘዴዎቹ ናቸው ። በመሆኑም ፣ ሌሎች ገጽታዎችን ወደጎን በመተው እነዚህና ለሌሎች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ኢኮኖሚያዊ ባህርያት ብቻ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል ። ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ኢኮኖሚያዊ ባህርያት ትኩረት የመስጠቱ አስፈላጊነት ባይካድም ፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ለመጠበቅ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥና ኃይሉን ለማጠናከር ፣ ሕግ ወይም የሕግ ቲየሪ የሚጫወተውን ሚና መዘንጋት ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በኅብረተሰባችን ውስጥ ገንኖ የሚታየው የውጭ ካፒታል የበላይነትና ፣ ሌሎችም ዓይነቶች ውጫዊ ቁጥጥሮች የሚከናወኑት በሕግ አማካይነት መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው ። ይህም የሕግ መዋቅር ፣ በኒኦ—ናችራሊዝም ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀና በሱም የሚደገፍ መሆኑን አሳይተናል ። ለምሳሌም ያህል ፣ የኻርት ቲየሪ ኒኦ—ናችራሊዝም ከቅኝ አገዛዝ ስላገኘው ልምድና ቅርስ ያለውን የተሳሳተ ፣ የተቆነጻጸለና ፤ የቀጨጨ እውቀት የሚያጠናክር ብቻ ሳይሆን ፣ የራሳችንን የሕግ ባህል ዝቅ አድርጎ የሚመለከትና የምዕራቡን የካፒታሊስት የሕግ ባህል የበላይነት ሊጭንብን የሚሞክር መሆኑንም ያሳያል ። ይህም በኅብረተሰባችን ውስጥ ከሚገኙ ከአቀባባይ ከበርቴውና ከወግ አጥባቂ ምሁራን ጋራ በግልጽና በምስጢር በመተባበር የውጭ ሕግ ቁጥጥር በኅብረተሰባችን እንዲሰፍንና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር በወደቀው ኅብረተሰባችን ላይ የካፒታል ቁጥጥርና የበላይነት እንዲረጋገጥ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ።

የኒኦ—ናችራሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ባህርይ ግልጽ ባልሆኑ መግለጫወች መጭበርበሩ ብቻ ሳይሆን ፣ ረቂቅ በሆኑ ቲየሪያዊ አባባሎች ( ቲየሬቲካል ፎርሙሌሽንስ ) ያጌጠም ነው ። የነዚህን ቲየሪዎች ዋና ይዘት ፈልፍሎ ለማውጣትና ፣ በቲየሪዎቹና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መካከል ያለውን ዝምድና ለማወቅ ፣ የነዚህን ቲየሪያዊ መርሆች እና የሕግ ረቂቅ ፈርጆች ( አብስትራክት ሊጋል ካቴጎሪስ ) መመርመር ይገባል ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ፣ ስለሕግ ማህበራዊ መሠረት ጥልቅና ሳይንሳዊ ትንታኔ ማድረግ ግድ ነው ። የሶስተኛው ዓለም አገሮችን ምዝብር ሕዝቦች አጠቃላይ ነጻነት ለማረጋገጥ ፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሕጎች የሚያስከትሉትን ውጤት ማወቅና ፣ ሌሎች ዘዴዎቹንም ማጋለጥ አስፈላጊ ነው ። ይህም ሲሆን ፣ የሶስተኛው ዓለም ሕዝቦች ከባዕድ ተጽዕኖና ቁጥጥር ለመላቀቅ የሚያደርጉት ትግል ከሁሉም አቅጣጫ ይፋፋማል ።

ደንቦች ሊባሉ ይችላሉ ። « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ማለት የልማድ ሕግ ደንብ ነው ብሎ ኻርት ቢቀበል ኖሮ ፤ ጥንታዊ ለሆኑት የቅኝ ግዛትና የቅድመ—ቅኝ ግዛት ኅብረተሰቦች የካፒታሊዝምን ሕጋዊነት ሊዋጉበት የሚያስችላቸውን የሕግ ሥልጣን መስጠቱ እንደነበር መገመት አያዳግትም ። በመሆኑም ፣ « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ን የሥልጣን መቀዳጃ ለሆነው ለሁለተኛ ደረጃ ሕግ ብቻ መወሰኑና ከ « ጥንታዊ ኅብረተሰቦች » ጋር አለማያያዙ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው ። ዋናው ምክንያት ይህ ነበር ( ይህ ደግሞ የኻርትን ቲየሪ መሠረታዊ ይዘት ያብራራል ) ኻርት የ « እውቂያ መስጫ ደንብ » ን የልማድ ሕግ ደንብ ነው ብሎ ሊጠራው ያልፈለገው ። ምክንያቱም « የእውቂያ መስጫ ደንብ » ሊሆን የሚችለው የ « ሕግ » ደንብ ነው ፤ በማለት ኻርት እንደምንም ብሎ « ጉዳዩን » የካፒታሊስት ሥርዓት የበላይነትና ደህንነት ጠብቋል ። ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝም ሕጋዊ ዋስትና ሰጥቷል ።

## ሐ/ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝና በኒኦ—ናችራሊዝም መካከል ስላለው ዝምድና

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ስላለው የሕግ አፈጣጠርና በተግባር አተረጓጎም ሁኔታ ፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ስላለው የአስማሚነት ሚና የተደረገው ትንተና ( አናሊስስ ) ምዕራባውያን የሕግ ሊቃውንትና ፈላስፋዎች አውቀው እንደፈጠሩት ነገር ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት ማስገንዘቡ ተገቢ ነው ። በተቃራኒው ፣ በምሁራን እና ቁሳዊ ምርት ( ኢንተለክቹዋል ኤንድ ማቴሪያል ፕሮዳክሽን ) መካከል ካለው ነባራዊ ግንኙነት እንደመነጨ ተደርጎ መታየት ይኖርበታል ። [59] ይህም ማለት ፣ በልዩ ልዩ የሕግ ሊቃውንት የሚገለፁ አስተሳሰቦች ፣ ጽንሰ—ሃሳቦችና ቲየሪዎች የካፒታሊስቱ ሥርዓት ነባራዊ ፍላጎቶች ውጤቶችና የካፒታሊስቱን የምርት ግንኙነት የሚያንጸባርቁ ናቸው ።

አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ግንኙነቶች በኅብረተሰቡ የገዥ መደቦች አመለካከቶች ይገለጻሉ ። [60] ነገር ግን ፣ ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው የሥራ ክፍፍል መሠረት እነዚህን ሃሳቦች የሚያፈልቁት የሕግ ሊቃውንት ናቸው። በመሆኑም ፣ የሕግ ሊቃውንቱ ረቂቅ ሃሳቦች ( አብስትራክት አይዲያስ ) ወይም « አይዲያል ፎርሙላ » በመጠቀም ለገዥው መደብ አስተሳሰቦች የሁለንተናዊነት ጠባይ በመስጠት እንደብቸኛና ፍጹማዊ ትክክለኛ ሃሳብ አድርገው ያቀርቧቸዋል ። በተጨባጭ ሲታይ ግን ፣ በነዚህ ሊቃውንት የሚፈልቁት ሃሳቦች ፣ ጽንሰ—ሃሳቦችና ፣ ቲየሪዎች ፣ በጊዜው ጎልቶ የሚታየው ቁሳዊ ግንኙነት መግለጫ ከመሆን አያልፉም ። ስለዚህ ፣ በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ የበላይነትን ባገኙ የሕግ ቲየሪዎች የሚገለጹት ሃሳቦች ሁሉ ፣ የካፒታሊስቱን የምርት ግንኙነትና የካፒታልን የበላይነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ። በዚህም ዓይነት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ከምሁራን የሚፈልቁት ሃሳቦች ሁሉ በተጨባጭ ከካፒታሊስቱ ሥልተ—ምርት ጋር ይዛመዳሉ ።

በመሆኑም በኒኦ—ናችራሊዝም የተገለጸው ፍትህ ፣ ነጻነት ፣ እኩልነት ፣ ሰብአዊ መብቶች ፣ ወዘተ ፣ የሚሉት ሃሳቦች ሁሉ ፤ በካፒታሊስቱ ማህበራዊ ግንኙነት ላይ የሚመሠረቱ ፣ የሚወሰኑና ፣ የሚቀየሩም ብቻ ሳይሆኑ ፣ የካፒታሊስቱን ሥርዓት ዓላማም ተግባራዊ ለማድረግ የታቀዱ ናቸው ። ለምሳሌም ፣ የቅኝ አገዛዝ የጭካኔ ድርጊቶች ለምን እንደወንጀል እንዳልተቆጠሩ ከዚህ ለመረዳት ይቻላል ። ምክንያቱም በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ እንደወንጀል የሚቆጠሩ ሁኔታዎች የሥርዓቱን ጥቅም የሚጻረሩ ብቻ ናቸው ። [61] የተፈጥሮ ሕግ ሊቃው

17. ምንም እንኳን አፍሪካውያን ከአውሮፓውያን ጋራ ከዚህ ጊዜ በፊትም ግንኙነት የነበራቸው ቢሆን ፡ ይህ ክፍለ ጊዜ ቅኝ አገዛዝ የገባበትና ደንበኛ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት የተጀመረበት ጊዜ ነው ። አዘግዌ ጂ ኤን ብሪትን ኤንድ ዘ ኮንከስት ኦቭ አፍሪካ ፡ ኤን ኦ ኢኑጉ (1983) ይመልከቱ ።

18. ስቶን ጂ ሊጋል ሲስተምስ ኤንድ ሎየርስ ሪዝኒንግስ ( ስቴቨንስ ኤንድ ሰንስ ፡ 1964 ) ገጽ 98 ፤ እና ሆል ጂ ስታዲስ ፡ በ ጁሪስፕሩደንስ ኤንድ ክሪምናል ቲየሪ ( 1958 ) ገጽ 35 ላይ የጻፈው ።

19. ዌቤር ኤም ሎ ኤንድ ኢኮኖሚ ኢን ሶሳይቲ ፡ ራይንሽቴይን ኤድሽን ( 1954 ) ምዕራፍ 12 እና 13 ፡ አልፐርት ፡ ኤሚል ዱርኬይም ኤንድ ሂዝ ሶሲዮሎጂ ( 1961 ) እና ኤሀርሊች ኢ ፡ ፈንዳሜንታል ፕሪንስፐልስ ኦቭ ሶሲዮሎጂ ኦቭ ሎ ፡ ሞል ኤም ዳብልዩ እንደተረጎመው ፡ ( ሃርቫርድ 1963 ) ይመልከቱ ።

20. ካመንካ ኢ እና ኒል ፡ አር ዴስ ኤድሽን ፡ ፊውዳሊዝም ፡ ካፒታሊዝም ኤንድ ብዮንድ ( ኤድዋርድ ኦርኖልድስ ፡ ፐርክሻዬር ፡ 1975 )

21. እንግሎ አሜሪካን ሪያሊዝም የተሰኘው ተፎካካሪ ቲየሪ ከሶስዮሎጂካል ጅሪስፕሩደንስ ጋራ ባንድ ወቅት አካባቢ ነው የተከሰተው ። የዚህ ቲየሪ ተጽዕኖ ግን በተባበሩት የአሜሪካግዛቶችና ስካንድኔቭያን አገሮች ብቻ የተወሰነ ነበር ።

22. ፓውንድ አር ፡ ጁሪስፕሩደንስ ( ዌስት ፡ ሳን ፓል ፡ 1959 )

23. ፓውንድ አር ፡ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ዘ ፍሎሶፊ ኦቭ ሎ ( ዬል 1961 )

24. ጃውሽች ኤል ኤስ ጀነራል ቲየሪ ኦቭ ሎ ( ፕሮግሬስ ሞስኮ 1981 ) « ሕጋዊ እውነታ» (ሊጋል ሪያሊቲ ) ማህበራዊ ህሊና ላይ ከሚመሠረቱ ማህበራዊ ንቃተ—ኅሊና ዓይነቶች አንዱ ነው ። ይሀም መሠረቱ ኢኮኖሚ የሆነ የሕግ ላዕላይ መዋቅር መሆኑ ነው ፤ ገጽ 10 ።

25. የቀውሱን ዝርዝር ሁኔታ ለማወቅ ቱማኖቭ ቪ ኤ ፡ ኮንቴምፖራሪ ሊጋል ቶውት ( ፕሮግሬስ ሞስኮ ፡ 1974 ) ይመልከቱ ።

26. ቦደንሜር ኢ ፡ " ፍሎሶፊካል አንትሮፖሎጂ ኤንድ ዘ ሎ "/ 1971/ ካሊፎርንያ ሎ ሪቪው ፡ ቅጽ 59 ፡ ቁጥር 3 ፡ ገጽ 653 ይመልከቱ ።

27. ፉለር ፡ ኤል ኤስ ዘ ሞራሊቲ ኦቭ ሎ ( ዬል 1964 ) ይመልከቱ ።

28. ኻርት ኤች ኤል ፡ ኢ ቡክ ሪቪው ፡ ሃርባርድ ሎ ሪቪው ( 1965 ) ገጽ 1284 ፤ እና ፉለር ኤል ኤስ ዘ ሞራሊቲ ኦቭ ሎ ፡ ሪባይዝድ ኤድሽን ( ዬል ፡ 1969 ) ፡ ምዕራፍ 5 ።

29. ኻርት ኤች ኤል ኤ ፡ ዘ ኮንሰፕት ኦቭ ሎ ( ኦክስፎርድ ፡ 1961 ) ገጽ 189—195 ።

30. ከላይ የተጠቀሰው ቦታ ።

31. ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ። ሕግ አንዳንድ ድርጊቶችን የሚከለክለው ፡ ድርጊቶቹ በራሳቸው ለሕሊና ተቃራኒ ስለሆኑ ሳይሆን ፡ ስሜትን የሚጐዱ ስለሆኑ ነው ፤ የሚል አቋም ይዞ የሚከራከረው ኻርት ፡ ሊጋል ፓተርናሊዝም በተሰኘው ቲየሪው ፡ የሕግ ዓላማ ሕዝቡን ከእንደዚህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች መጠበቅ ነው ብሏል ። ኻርት ኤች ኤል ሎ ፡ ሊበርቲ ፡ ኤንድ ሞራሊቲ ፡ ( ኦክስፎርድ 1963)።

32. ሎክ ሕግ ማህበራዊ ግንኙነቶችንና ምርትን የሚዳኝ ገለልተኛ መዋቅር ነው ይላል ። በርሱ አባባል መንግሥት አስፈላጊውን ጥበቃ መስጠት አለበት ( ይህ በሆብስ ቲየሪ ውስጥ የለም ) ፤ ነገር ግን ፡ ተግባሩ ግለሰቡ ደህንነቱን ( ማለትም ንብረቱን ) የሚያስጠብቅበትን ግንኙነት መፍቀድ ነው ። ሰዎች ራሳቸውን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚያደርጉበት ዓይነተኛ ዓላማ ንብረታቸውን ለመጠበቅ ነውና» ። ሎክ ጂ ሲቪል ገቨርንመንት ፡ ሰከንድ ትሪቲዝ ፡ ጉፍ ኤድሽን ( 1946) ምዕራፍ 9 ።

33. ኻርትና ሳክስ ዘ ሊገል ፕሮሰስ—ቤዚክ ፕሮብሌምስ ኦን ዘ ሜኪንግ ኤንድ አፕሊኬሽን ኦቭ ሎ ፡ ቱንዝ ኤድሽን ( 1958 ) ከገጽ 124—185፣

34. « ነጻ ንግድ » ማለት ከማንኛውም ፖለቲካዊ ፡ ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ጫና የነጻና « በዘላለማዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሕጎች » ብቻ የሚገዛ የካፒታል እንቅስቃሴ ማለት ነው ። ይህም ማለት ካፒታል የሚራባበትና የሚከፋፈልበት ሁኔታ ማለት ነው ። ካርል ማርክስ « ዘ ቻርትስትስ » ኒው ዮርክ ዴይሊ ትሪቡን ( 25 ኦገስት 1852 ) ይመልከቱ ።

35. ይህ ሃሳብ በአሜሪካን ጁሪስፒሩደንስ ውስጥ ያለውን « ሩል ኦቭ ሎ » የሚባለውን ጽንሰ—ሃሳብ ይመስላል ፤ ወይም የዚህን ጽንሰ—ሃሳብ ማብራሪያ ይወክላል ሊባል ይቻላል ።

36. ፍሬድማን ፡ ሎ ኢን ቼንጂንግ ሶሳይቲ ፡ ሁለተኛ እትም ፡ / ስቲቨንስና ልጆቹ ፡ 1972 / የሁለተኛ እትም መቅድም ገጽ 11 ይመልከቱ ። እንዲሁም ማክዱጋል ኤም " ኢንተርናሽናል ሎ ፡ ፓወር ኤንድ ፖሊሲ ኤንድ ኮንቴምፖራሪ ኮንሰፕሽን" 82 ሬኩይልዴኩር/1953/ገጽ 183 ይመልከቱ ።

37. ጂሱፕ ፒ ሲ ፡ ትራንስናሺናል ሎ / ዬል 1956 / ገጽ 51

38. በቱንኪን መጽሐፍ ውስጥ ያለውን አድሀሪ የኢንተርናሽናል ሕግ ደንቦችን ( ኖርምስ) ላለመቀበል የሶቭዬት ኅብረት ያደረገችውን ክርክር—ቱንኪን ጂ አይ ፡ ቲየሪ ኦቭ ኢንተርናሽናል ሎ ፡ በተር ደብልዩ ኢ. እንደተረጐመው ( ሃርባርድ 1974 ) ክፍል 1 ፡ ምዕራፍ 2

39. ናክሩሼር ቪ ኒኦ— ኰሎኒያሊዝም ፡ ሜተድስ ኤንድ ማኑቨርስ ( ፕሮግሬስ ፡ ሞስኮ ፡ 1973) ገጽ 47

40. በዚህ ዘመን የነበሩትን የተፈጥሮ ሕግ ጸሐፊዎችን ዝርዝር ለማግኘት ኢንሳይክሎፔድያ ኦቭ ፍሎሶፊ ፡ የኤድዋርድስ እትም ( ፒ፡ ማክሚላን 1976) ይመልከቱ ።

41. ኡምዞርኬ ዩ ሲ ፡ ኢንተርናሽናል ሎ ኤንድ ኰሎኒያሊዝም ኢን አፍሪካ ንዋምፌ ኢኑጉ ( 1979 — ጽሑፉ የቅኝ አገዛዝን ፍትሀ አልባነትና « ሕገ—ወጥነት »ለማጋለጥ የሚደረገውን ጥረት ያስረዳል ።

42. ቱንኪን ፡ ከላይ በተጠቀሰው ሥራው ክፍል 3 ፡ ምዕራፍ 9 ይመልከቱ ።

43. ከላይ በተጠቀሰው ሥራ ፡ ገጽ 264

44. ሻርዘርንበርገር ጂ ፡ ኢንተርናሽናል ሎ ፡ ስቲቨንስ 3ኛ እትም ( 1957 ) ገጽ 186

45. ይሀ ለተፈጥሮ ሕግ ቲየሪ የተሰጠ ምላሽ ነው ። ፖዘቲቭዝም የተፈጥሮ ሕግን እንደ የሕግ ሥርዓት አይቀበለውም ። ምክንያቱም ሁም እንዳስቀመጠው « የተፈጥሮ ሕግ ትክክለኛነት በተጨባጭ ሎጅክ የሚገለጽ ሳይሆን ፡ ቲየሪውን በሚቀበሉ ሰዎች አንጻራዊ አመለካከት የሚወሰን ነው »። ሁምዲ፡ ኤ ትሪቲዝ ኦቭ ሂዩማን ኔቸር፡ ሲ.ኤ.ቢ. ቢግ ኤድሽን (1888) ከገጽ 516—534 ይመልከቱ። በሌላ በኩል ፡ ፖዘቲቭ ሎ ምንም ኅሊናዊ ግምት ሳይታከልበት የሚረጋገጥና ትክክለኛ ነው ። በመሆኑም ከተፈጥሮ ሕግ ጋራ አንድ ነው ተብሎ ከሚገመተው ሞራሊቲ ጋራ ሲነጻጸር ፖዘቲቭ ሎ የተለየ ነው ።

46. ኻርት ኤች ኤል ኤ ፡ « ፖዘቲቭዝም ኤንድ ዘ ሴፖሬሽን ኦቭ ሎ ኤንድ ሞራልስ » ( 1958 ) 71 ሃርባርድ ሎ ሪቪው 593 ጥሩ ሥርዓት ማለት ከፍትሀ ጥያቄ ጋር የሚሄድ ነው ወይም መሆን አለበት ብለው ሰዎች የሚያስቡት ነው ለሚለው በፉለር የተሰጠ መልስ ። ፉለር ኤል ኤ « ፖዘቲቭዝም ኤንድ ፍዴሊቲ ቱ ሎ — ለፕሮፌሰር ኻርት የተሰጠ መልስ » ( 1958 ) 71 ፡ ሃርባርድ ሎ ሪቪው ገጽ 630

47. በምዕራቡ ዓለም የሕግ ፍልስፍና ወንጀል የሚባለው በአዋጅ ( በሕግ ) ወንጀል ነው ተብሎ የተደነገገ ነገር እንጂ ማንኛውም ክፉ ተግባር አይደለም ። « ፍትሀ በሕጉ መሠረት» የሚለው መርሀ በፍትሀ አስተዳደር ውስጥ ሞራል ቦታ እንደሌለው ያመለክታል ።

48. ኻርት ኤች ኤል ኤ ፡ ዘ ኰንሰፕት ኦቭ ሎ ገጽ 92 ።

49. እላይ የተጠቀሰው ሥራ ፡ ምዕራፍ 6

50. እላይ የተጠቀሰው ሥራ ፡ ገጽ 105 ። በአፍሪካ ውስጥ ለልማድ በሚሰጠው ትርጉም ላይ ይሀ ሁኔታ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል ። ኤልያስ ቲ ኦ ፡ ዘ ኔቸር ኦቭ አፍሪካን ክስተሜሪ ሎ ምዕራፍ 2 እና 5ን ይመልከቱ ።

51. ኻርት ኤች ኤል ኤ ፡ ዘ ኰንሰፕት ኦቭ ሎ ፡ ገጽ 107

52. ከላይ የተጠቀሰውው ቦታ

53. ኻርት ራሱ በገጽ 16 ላይ እንደሚያምነው እነዚህን ኅብረተሰቦች « ጥንታዊ » ብሎ ለመመደብ ምንም ታሪካዊ መሠረት እንደሌለ ማወቁ ጠቃሚ ነው ። የመዋቅር ጉድለቶችን እንደምሳሌ ልመጥቀስ ፡ ( ለምሳሌ ለውጥ የማይታይባቸው / ስታቲክ) በማለት የተደረገው አስመሳይ ጥረትም ማረጋገጫ አልቀረበበትም ። ይሀ በዘፈቀደ የተደረገ አመዳደብ የአውሮፓውያንን የተሳሳተ አመለካከት ጥንታዊ በሆኑ የቅኝ ግዛትና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች ላይ ለመጫን እንደተደረገ ጥረት ብቻ መታየት የለበትም ።

54. ራዝ ጂ « ዘ አይደንቲቲ ኦቭ ሲስተምስ » 59 ካሊፎርኒያ ሎ ሪቪው ( 1971 ) ገጽ 795

55. ኻርት ኤች ኤል ኤ ፡ ዘ ኰንሰፕት ኦቭ ሎ ፡ ገጽ 89—93

56. ከላይ የተጠቀሰው ፡ ከገጽ 93—96

57. ከላይ የተጠቀሰው ቦታ ።

58. ከላይ የተጠቀሰው ሥራ ፡ ገጽ 92 ። እንዲሁም በገጽ 3 ላይ ይመልከቱ ። ኻርት አንዳንድ አገሮችን በስም ጠርቶ « የሕግ » ኅብረተሰቦች ብሎ ሲመድብ « ቅድመ—ሕግ »ኅብረተሰቦችን « ጥንታዊ » ብሎ በመሰየሙ የራሱን ግብዝ አመለካከት ያጋልጣል ። እነዚህን ኋለኞቹን በስም ለመጥራት አልተቸገረበትም ። በሌላ በኩል ፡ « አገሮች » የሚለውን ስም ለ « ሕግ » ኅብረተሰቦች በመመደቡ ፡ ኻርት ትክክል ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ « ቅድመ—ሕግ» ኅብረተሰቦች አብዛኞቹ ገና ቅኝ ግዛቶች ነበሩና ።

59. ይህ በማርክስና በኤንግልስ የዳበረ ሳይንሳዊ ጽንሰ—ሃሳብ ነው ። በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ቁሳዊ ምርትን እንደአጠቃላይ ፈርጅ ( ጄነራል ካቴጎሪ ) ሳይሆን ፣ የራሱ የሆነ ታሪካዊ ቅርጽ እንዳለው ተደርጎ መታየት አለበት ። ይህ ከተደረገ፣ ከቁሳዊ ምርት ጋራ ጎን ለጎን የሚሄደውን ምሁራዊ ምርትና በሁለቱም መካከል ያለውን መተሳሰር መረዳት እንችላለን »። ማርክስ — ኤንግልስ ጀርመን አይዴዮሎጂ ፣ ቅጽ 5 ( ፕሮግሬስ ፣ ሞስኮ ፣ 1854—46 )ክፍል 1 ፣ ከገጽ 35—37

60. ይህም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ቁሳዊ የበላይነት ያለው መደብ ምሁራዊ የበላይነትም ይኖረዋል በሚል የሐቅ ግምት ላይ የተመሠረተ ነው ። የማርክስና የኤንግልስን ጀርመን አይዲዮሎጂ ገጽ 36 ይመልከቱ ።

61. ይህ ሁኔታ የባርያ ጉልበት በካፒታሊዝም ሥርጸትና እድገት ላይ የተጫወተውን ሚና በማስመልከት ማርክስ ባካሄደው ጥናት በሰፊው ተብራርቷል ። በጥናቱ እንደተገለጸው የባርያ ጉልበት ለሥርዓቱ እድገት አስፈላጊ በነበረበት ወቅት እንደ አንድ በሕግ የተደገፈ የንብረት አያያዝ መልክ ይጠበቅ ነበር ። በመሆኑም የባርነት ኢሰብአዊ ገጽታ እንደሕገ—ወጥ ድርጊት አልተቆጠረም ነበር ። ባርነት ሕገ—ወጥ ድርጊት ነው ተብሎ የታወጀው አብዛኛው በባርያ ጉልበት ይከናወኑ የነበሩት ሥራዎች በማሽንስ ከተተኩና የሰው ጉልበት ለተሻለ የካፒታሊስት እድገት አስፈላጊ መሆኑ ከቀረ በኋላ ነበር ። ማርክስና ኤንግልስ ቅጽ 1 ፣ ገጽ 465 ይመልከቱ ።

62. « ምሁር » ( እሊት ) የተሰኘው ቃል እዚህ የገባው በማርክሳውያን አጠቃቀም ትርጉሙ ነው ። በዚህም መሠረት ምሁራን እንድን ማህበራዊ መደብ የሚወክሉና በማህበራዊ ምርት ውስጥ ራሱን የቻለ ቦታ ያላቸው ሳይሆኑ ፣ ጥቅማቸውን ከሚጠብቁላቸው መደቦች ጋራ የተቆራኙ ወይም በምስጢር የሚተባበሩ ናቸው ።

63. ለምሳሌ ያህል ፣ በአሁኑ ጊዜ በናይጄሪያ ውስጥ በአብዛኛው የእንግሊዝን ሕግ ብቻ ገልብጠው የሚያቀርቡት የሕግ መማሪያ መጻሕፍት ጉልህ ማስረጃዎች ናቸው ።